## ምዕራፍ ፡ ፺፯ ።

### የቦረን ፡ ልጆች ።

፩ ፤ ደጨ ፡ ጅሌ ፡ ክኖ ፡ በቾ ፡ እኒህ ፡ ቱለማ ፡ ይባላሉ ። አካኮ ፤ ወበ ፡ ሉባ ፤ እኒህ ፡ ሰደቻ ፡ ይባላሉ ። ጭሌ ፤ ሊበን ፡ ጉድሩ ፡ ሆኮ ፤ እኒህ ፡ ሆኮ ፡ ይባላሉ ። እነዚህ ፡ ፲፩ዱ ፡ የቦረን ፡ ልጆች ፡ ፳ ፡ ልጆች ፡ ወለዱ ። ስማቸውም ፡ የደጨ ፡ ልጆች ሌቃ ፤ ጨለባ ፤ የጅሌ ፡ ልጆች ፡ ወለጋ ፤ ጉማ ፤ የክና ፡ ልጆች ፡ ሊሙ ፤ ጅማ ፤ ጌራ ፤ የበቾ ፡ ልጆች ፡ አብቹ ፤ ግምብቹ ፤ የአካኮ ፡ ልጆች ፡ ወበሪ ፤ ገላን ፤ የወበ ፡ ልጆች ፡ ሉሜ ፤ ሊበን ፤ የሉባ ፡ ልጆች ፡ ሜታ ፤ ቀዩ ፤ የጭሌ ፡ ልጆች ፡ ጉለሌ ፤ ሰላሌ ፤ የሊበን ፡ ልጅ ፡ አብቲ ፤ የጉድሩ ፡ ልጅ ፡ ዱራ ፤ የሆኮ ፡ ልጅ ፡ ቦረና ፤ እነዚህ ፡ የቦረን ፡ ልጆች ፡ ፳ ፡ የበርቱማ ፡ ፳፯ ፡ በድምሩ ፡ ፵፯ ፡ ቀኖች ፡ የጋላ ፡ አባቶች ፡ ናቸው ።

፪ ፤ እነዚህም ፡ በፍጥነት ፡ ተራቡና ፡ እጅግ ፡ በዙ ። ከብዛታቸውም ፡ የተነሣ ፡ እየገፉ ፡ ክርስቲያኑን ፡ እያጠፉና ፡ እያቃጠሉ ፡ የክርስቲያኑን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ወረሱ ። በኢትዮጵያ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳትና ፡ ጥፋት ፡ የሆነው ፡ በነገሥታቱ ፡ ቸልተኝነት ፤ በመኳንንቱ ፡ ትዕቢትና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ፍቅር ፡ በማጣት ፤ በሕዝቡም ፡ እርስ ፡ በርሱ ባለመስማማትና ፤ በመለያየት ፡ መንግሥቱ ፡ ደክሞ ፡ አገርም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ በሁከት ፡ ተበላሽቶ ፡ ብርቱ ፡ ኃይል ፡ የሚሆነው ፡ አንድነትና ፡ መስማማት ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ ነው ።

፫ ፤ ዛሬ ፡ ጋላ ፡ የያዘው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ጥንት ፡ የክርስቲያን ፡ አገር ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከሐረር ፡ እስከ ፡ በላያና ፡ እስከ ፡ ቦረና ፤ ከከፋ ፡ እስከ ፡ ራያና ፡ አዘቦ ፡ ባለው ፡ ጋላ ፡ በያዘው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፤ የከተማና ፡ የከበሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የኖራ ፡ ግንብ ፡ ፍራሽ ፤ የንዋየ ፡ ቅድሳት ፤ የፃሕል ፡ የዐውድ ፤ የመስቀል ፡ የአክሊል ፤ የመቋሚያ ፤ የጸናጽል ፤ ስባሪና ፡ ሌላም ፡ ሁሉ ፡ ከፍርስራሹ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ የኖረው ፡ አፈር ፡ በልቶት ፡ በቅርቡ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ተገኝቷል ። ደግሞም ፡ ጋላ ፡ ሲዘርፋቸው ፡ በየዋሻው ፡ ሸሽገው ፡ ያኖሯቸው ፡ ብዙ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አልባሳት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከመኖራቸው ፡ የተነሣ ፡ ብል ፡ በልቶአቸው ፡ የሌት ፡ ወፍ ፡ ቀዳዶአቸው ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳትና ፡ መጻሕፍትም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እየተመረመሩ ፡ ይገኛሉ ።

### ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገዴ ፡ ቦረን ፡ የሚባሉት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ፡ ? የቦረንን ፡ ልጆች ፡ ስማቸውንና ፡ ቊጥራቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ፤ በድምሩ ፡ የጋላ ፡ አባቶች ፡ ስንት ፡ ናቸው ፡ ? ስማቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።

፪ ፤ ጋሎች ፣ የክርስቲያን ፣ አገር ፣ የነበረችውን ፣ ኢትዮጵያን ፣ የወረሱ ፤ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ?

፫ ፤ ዛሬ ፣ ጋላ ፣ የያዘው ፣ አገር ፣ ጥንት ፣ የክርስቲያን ፣ አገር ፣ መሆኑን ፣ በምን ፣ ታስረዳለህ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፶፫ ።

### ነገደ እናርያ ።

፩ ፤ የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ የካም ፣ ዘር ፣ ነው ። ነገዱ ፣ ዮቅጣን ፣ መጥተው ። የነገዱ ፣ ኩሳን ፣ መንግሥት ፣ ወስደው ፣ ሕዝቡን ፣ በጦር ፣ አጥፍተው ፣ የተረፈውንም ፣ ባሳደዱ ፣ ጊዜ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ደቡብ ፣ ዳር ፣ ለዳር ፣ በወላሞ ፤ በሲዳሞ ፤ በኩሎ ፤ በኮንታ ፤ በአማሮ ፤ በጃንጅሮ ፤ የሚኖር ፣ ሕዝብ ፣ ነው ። ከጦርነቱም ፣ በኋላ ፣ ከነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ ገብቶ ፣ ለነርሱ ፣ እጅ ፣ ነስቶ ፤ ተገዝቶ ፤ ታዝዞ ፤ ገብሮ ፣ የሚኖር ፣ ነው ። ጋሎች ፣ ሳይዙት ፣ አስቀድሞ ፣ ሉቅማ ፤ ጅማ ፤ ሌቃ ፤ ትቤ ፤ ከፋ ፤ ይህ ፣ ሁሉ ፣ የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ አገር ፣ ነበር ።

፪ ፤ ይህ ፣ ሁሉ ፣ ከቀድሞ ፣ ጀምሮ ፤ እስከ ፣ ቀዳማዊ ፣ ምኒልክ ፣ ዘመን ፤ ከዚያም ፣ በኋላ ፣ እስከ ፣ ዘመነ ፣ ክርስትና ፣ ተያይዞ ፣ እንደ ፣ መጣ ፣ አንድ ፣ እናርያ ፣ ተብሎ ፣ ከንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ በታች ፣ አንድ ፣ ንጉሥ ፣ ይሾምበትና ፣ ይነግሥበት ፣ ነበር ።

፫ ፤ ይህም ፣ ሊታወቅ ፤ ስለ ፣ ቀዳማዊ ፣ ምኒልክ ፣ በሚናገረው ፣ ዙዋይ ፣ በተገኘው ፣ ታሪክ ፤ አብሂል ፣ ከብንያም ፣ ነገድ ፣ አልጋውና ፣ ዙፋኑ ፣ ከብር ፣ የተሠራለት ፣ ንጉሥ ፣ ነበር ። ግዛቱም ፣ ሉቅማ ፤ ጅማ ፤ ሌቃ ፤ ትቤ ፤ ጉማ ፤ ከተማውም ፣ ከፋ ፣ አገር ፣ እናርያ ፣ ነው ። እርሱም ፣ ለንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ይታዘዛል ፣ በማለቱ ፣ ይታወቃል ።

፬ ፤ የእናርያ ፣ ከተማ ፣ የወላሞ ፣ ዳሞት ፣ ሀዲያ ፣ ኪንዶ ፤ ወይም ፣ ሀንድ ፣ የሚባል ፣ ነበር ። ቀድሞ ፣ ተጠቅልሎ ፣ በንድ ፣ ንጉሥ ፣ ይገዛ ፣ ነበር ። እንደ ፣ ገበዘ ፣ አክሱም ፣ ሊቀ ፣ ካህናቱ ፣ የዠንጅሮ ፣ ንጉሥ ፣ ነበር ። ባረብኛ ፣ ዠን ፣ ማለት ፣ ባለግርማ ፣ የሚያንቀጠቅጥ ፣ ማለት ፣ ነው ። ጅሮ ፣ ማለት ፣ ድሮ ፣ ማለት ፣ ይመስላል ። ስለዚህ ፣ ዠንጅሮ ፣ ማለት ፣ የድሮ ፣ ባለግርማ ፣ ንጉሥ ፣ ማለት ፣ ይሆናል ። እርግጡ ፣ ግን ፣ አልታወቀም ።

፭ ፤ የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ ባጼ አግብዓ ፣ ጽዮን ፣ ዘመን ፣ በሺ ፣ ፪፻፸ ፣ ዓመተ ፣ ምሕረት ፣ በአቡነ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ ስብከት ፣ አምኖ ፣ ተቀብሎ ፣ ክርስቲያን ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። ብኋላ ፣ ግን ፣ የኢትዮጵያ ፣ ነገሥታት ፣ ኀይል ፣ እየደከመ ፣ እያጠረ ፤ ወደ ፣ ኋላ ፣ እያለ ፣ በሔደ ፣ ጊዜ ፤ ጋላ ፣ ወረሳ ፣ እየመታ ፤ አገሩን ፣ እየወረረ ፣ መምህራኑንና ፣ ካህናቱን ፣ እየገደለ ፤ መጽሕፍቱንና ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናቱን ፣ እያቃ

ጠለ ፡ ቢያጠፋው ፡ ከሞት ፡ የተረፈውም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያስተምረው ፡ ቢያጣ ፡
እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሶ ፡ አረማዊ ፡ ሆንና ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ አጥፍቶ ፡ በዘ
ንዶና ፡ በዛር ፡ አመለከ ። የእናርያ ፡ አገር ፡ ጥንት ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሚ
ያስረዳ ፡ ዛሬውኑ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንፃ ፡ ፍርስራሽ ፤ የመ
ስቀልና ፡ የጽና ። ሌላም ፡ ሌላም ፡ የንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ስባሪና ፡ ምልክት ፡
የመጻሕፍትም ፡ ቍራጭ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ይገኛል ፤ ባንዳንድ ፡ ስፍራም ፡ በየዋ
ሻው ፡ ታቦታቱ ፤ መጻሕፍቱ ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፤ አልባሳቱ ፤ ሁሉ ፤ ይገኛሉ ።

፮፤ ክርስትና ፡ ከጠፋባቸው ፡ ወዲህ ፡ የእናርያ ፡ ሕዝብ ፡ በዘንዶና ፡ በዛር ፡ እንዳ
መለኩ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የሚነግሥ ፡ የጃንጅሮ ፡ ንጉሥ ፡ ለዘንዶ ፡
ይገብራል ። ንጉሡም ፡ ባለብዙ ፡ ሚስት ፡ ነው ። ደግሞ ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ችውን ፡ የጨዋ ፡ ወገን ፡ የምትባለውን ፡ የባለጌም ፤ የድኃም ፤ የባለጸጋም ፤ ልጅ
ብትሆን ፡ ሳይለይ ፡ ይደርስባታል ። ብዙም ፡ ይወልዳል ። ንጉሡም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡
ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ይሰበስቡዋቸዋል ። ፶ም ፡ ፷ም ፡ እስከ ፡ ፪ም ፡ ቢሆኑ ፡ ወደ ፡ ዘን
ዶው ፡ ቦታ ፡ ይወስዱቸዋል ። መናገሻው ፡ ከዚያ ፡ ነውና ፤ ልጆችም ፡ ከዚያ ፡
ባንድ ፡ ቦታ ፡ ይቀመጣሉ ። ያልታወቁም ፡ ልጆች ፡ በዚያን ፡ ሌሊት ፡ ይመጣሉ ።
እናቶቻቸው ፡ እኛም ፡ ከንጉሡ ፡ ነው ፡ የወለድናቸው ፡ እያሉ ፡ ያመጧቸውና ፡
ያቀላቅሉዋቸዋል ። ብዙ ፡ ከብትም ፡ በያይነቱ ፡ ይታረዳል ። የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ
ሁለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ የሚሆን ፡ ከልጆቹ ፡ ርቆ ፡ ቁሞ ፡ ከልቡ ፡ እየጮኸ ፡
በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዜማ ፡ እየዘፈነ ፡ ይጨፍራል ። ጩኸቱና ፡ ዘፈኑ ፡ ማጉራቱም ፡ በደ
መቀ ፡ ጊዜ ፡ ዘንዶው ፡ ከጕሬው ፡ መዘዝ ፡ ብሎ ፡ ይወጣና ፡ ከታረደው ፡ ከደሙ ፡
ሁሉ ፡ ይቀምሳል ።

፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከልጆቹ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ይጠመጠማል ። የቀሩት ፡ ወንድ
ሞቹ ፡ ፈጥነው ፡ ተነሥተው ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ፡ ይሰግዳሉ ። ከሩቅ ፡
ያለውም ፡ ዘፋኙና ፡ ጨፋሪው ፡ ሕዝብ ፡ እየሮጠ ፡ ይቀርብና ፡ እየተደፋ ፡ ይሰ
ግዳል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ቀቢው ፡ ዘንዶ ፡ ተተርትሮለት ፡ ይሄድና ፡ ከጕሬው ፡ ይገባል ።

፰፤ ይህ ፡ የተቀባ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣና ፡ ሕዝቡንም ፡ ተነሥ ፡ ይለዋል ። ሕዝቡም ፡
ተነሥቶ ፡ ይሰግድለታል ። የቀሩት ፡ ወንድሞቹ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡
ሕዝቡ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከንጉሥ ፡ ዘር ፡ ቍጥር ፤ የላቸውም ። የሰጊዱን ፡ ሥር
ዓት ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ወጉ ፡ ግብር ፡ ይገባና ፤ ያ ፡ የታረደው ፡ ሥጋ ፡
ቀርቦ ፡ ይበላል ። የተረፈውንም ፡ ከቤት ፡ አያገቡትም ። ሥርዓታቸውና ፡ ወጋ
ቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከዚያው ፡ ጥለውት ፡ ይሄዳሉ ።

፱፤ የተሰበሰበው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጕሣና ፡ ነገድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሚበላውን ፡ እንደ ፡ ጠባይ ፡
እንደ ፡ ጠባዩ ፡ ያቀርቡለታል ። ይኸውም ፡ አማሮችና ፡ ትግሬዎች ፡ የእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የሹልዳ ፡ ሥጋ ፡ አይበሉም ። ይልቁንም ፡ ነገሥታትና ፡ የነገሥ
ታት ፡ ዘር ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ አይበሉም ። እርማቸው ፡ ነው ። በአሬት ፡ ዘፍጥ

ረት፡ምዕ፴፪፡ቍ. ፴፪ ፡ እንደ፡ተጻፈ ፤ እግዚአብሔር፡የያዕቆብን፡ጭን(ሹልዳ፡) ዳስሶ
አፍዝዞታልና ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሹልዳ
አይበሉም ። ሹልዳ ፡ አንበላም ፡ በማለታቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መሆናቸ
ውን ፡ ይመሰክራሉ ።

፲ ፤ እንዲሁም ፡ እኩሉ ፡ በፋት ፤ ወይም ፡ ዳሞት ፡ የሚባሉት ፡ የእናርያ ፡ ሕዝብ ፡ ፍየል ፤
በግ ፤ ዶሮ ፤ ዓሣ ፤ ተልባ ፤ የማይበሉም ፡ አሉ ። በየጠባያቸው ፡ ያቀርቡላቸዋል ፡
የተባለው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። እንዲሁ ፡ በየካህናታቸውና ፡ በየዛር ፡ ፈረሱ ፤ በየቃል
ቻው ፡ እንደ ፡ ወጉ ፡ ይቀርብላቸዋል ።

፲፩ ፤ ይህን ፡ መሥዋዕት ፡ በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ ከዚያው ፡ ጥለው
ንጉሡን ፡ አጅበው ፡ እየዘፈኑ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ያገቡታል ። እርሱም ፡ ከቤቱ ፡
ገብቶ ፡ ከዝሙት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የለውም ።

፲፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዙሪያው ፡ ያሉ ፡ ነገሥታት ፡ መልእክተኞቻቸውን ፡ ወደርሱ ፡
ይልካሉ ። ሕያው ፡ ንጉሥ ፡ ለማለትና ፡ ከመንፈሱ ፡ እንዲልክላቸው ፤ በረከቱም ፡
እንዲደርሳቸው ፡ በየመንግሥቱ ፡ ያለው ፡ የዛር ፡ አለቃ ፡ ሁሉ ፡ ይሄድና ፡ ከንጉሡ ፡
ዘንድ ፡ ይበረካል ፡ በዘንዶ ፡ መጠምጠም ፡ የለዘበ ፡ ገላውን ፡ ይዳስስና ፡ እጁን ፡ ጨብጦ ፡
ከሰው ፡ ሳይነጋገር ፡ ወዳገሩ ፡ ንጉሥ ፡ በግሥገሣ ፡ ይደርሳል ። የንጉሡንም ፡ ገላ ፡
በዚያ ፡ በእጁ ፡ ይዳስስና ፡ ከእጁ ፡ እንዳይቀር ፡ ከንጉሡ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡
በውሃ ፡ ይታጠባል ።

፲፫ ፤ ይህ ፡ ሥርዓት ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ እስከ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡
ይደረግ ፡ ነበር ። የሚልኩትም ፡ ነገሥታት ፡ የከፋ ፤ የኰሎ ፤ የኰንታ ፤ የከም
ባታ ፤ የወላሞ ፤ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ በዙሪያው ፡ ያሉ ፤ አገሮች ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።

፲፬ ፤ በዚያው ፡ ንጉሡ ፡ በተዳሰሰበት ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ይደረጋል ። የዛር ፡
ዘፈን ፡ ይዘፈናል ። በነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ የሚሾመው ፡ የዛር ፡ አለቃ ፡ በሴትና ፡
በግዛት ፡ እየተቃኑ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ አይፋቀሩም ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡
በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የነገሠ ፡ የከፋ ፡ ንጉሥ ፡ ከሮየሮ ፡ የተባለው ፡ ከዛንጅሮ ፡ ከተ
ቀበ ፡ በኋላ ፡ የዛርንም ፡ አለቅነት ፡ ጨምሮ ፡ ይዞ ፡ ንጉሥና ፡ የዛር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡
ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹና ፡ የቀሩትም ፡ ነገሥታት ፡ የዛር ፡ አለቅነትን ፡
ደርበዋል ።

፲፭ ፤ ዛርን ፡ የሰደበ ፡ የሚፈረድበት ፡ ከዛንጅሮ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በተፈረደ
በትም ፡ ጊዜ ፡ ለዘንዶው ፡ ይሰጥና ፡ ይውጠዋል ። ጥንት ፡ ነገሥታቱ ፡ ክርስቲ
ያኖች ፡ ሳሉ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ አሳልፈው ፡ አይሰጡም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡
አረማውያን ፡ ሁነው ፡ የዛር ፡ አለቅነትን ፡ ከደረቡ ፡ በኋላ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡ ፡ ጀመር ።

፲፮ ፤ አስቀድመን ፡ እንደጻፍነው ፡ በዘመነ ፡ ክርስትና ፡ የክርስቲያን ፡ ጨዋ ፡ ወታ
ደር ፡ በእናርያ ፡ ተሠራበትና ፡ ከክርስቲያን ፡ ተቋርጦ ፡ የቀረ ፤ የቄሱ ፡ ልድ ፡
ቄስ ፤ የሹሙ ፡ ልጅ ፡ ሹም ፤ የጨዋው ፡ ልጅ ፡ ጨዋ ፡ እየሆነ ፡ በተሠራበት ፡
አገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ እንደዚሁም ፣ ሁሉ ፣ ሠንጋ ፣ በካ ፣ በላይ ፣ ብለት ፣ በምትባል ፣ አገር ፣ ትንሽ ፣ ኮረፍታ ፣ አለች ። ዛሬ ፣ የአቡነ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ ታቦት ፣ ተተክሎበታል ። ጥንት ፣ በዚያ ፣ ስፍራ ፣ ታላቅ ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ ቤተ ፣ ደስክ ፣ የሚባል ፣ የዛር ፣ መቅደስ ፣ ነበር ። የክርስቲያን ፣ ነገሥታትና ፣ መኳንንት ፣ ዘመቻ ፣ ሲነሡ ፣ ከዚያ ፣ ይሰፍሩና ፣ ከዛሩ ፣ አለቃ ፣ ምክር ፣ ተቀብለው ፣ ይዘምቱ ፣ ነበሩ ፤ በአገሩም ፣ የነበሩ ፣ የጋፋት ፣ ሕዝብ ፣ አምልኮዋቸው ፣ በዚህ ፣ ቤተ ፣ ደስክ ፣ ነበረ ። ይህንንም ፣ ቤተ ፣ ደስክ ፣ በኋላ ፣ አቡነ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ አፈረሱት ፣ ይባላል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ የማን ፣ ዘር ፣ ናቸው ፣ ? የሚኖሩበት ፣ ክፍል ፣ በየት ፣ ነው ፣ ?
፪ ፤ የእናርያ ፣ ከተማ ፣ ማን ፣ ይባል ፣ ኖሮዋል ፣ ?
፫ ፤ የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ ክርስቲያን ፣ የነበረው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? የእናርያ ፣ ሕዝብ ፣ ክርስቲያን ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ በምን ፣ ታስረዳለህ ፣ ?
፬ ፤ ክርስትናን ፣ ከተዉ ፣ በኋላ ፣ በምን ፣ ያመልኩ ፣ ኑረዋል ፣ ? ልማደ ፣ ሀገራቸውን ፣ ዘርዝረህ ፣ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፣ ፲፪ ።

### ነገደ ፣ እስላም ።

፩ ፤ በ፮፻፳ ፣ ዓ. ም. በምሥራቅ ፣ አገር ፣ በእስያ ፣ የእስላሞች ፣ ነቢይና ፣ ንጉሥ ፤ ሙሐመድ ፣ ተነሣና ፣ የምሥራቅን ፣ አገር ፣ ገለባበጠ ። ወደ ፣ ሐበሻ ፣ ግን ፣ አልቀረበም ። ነገር ፣ ግን ፣ በዐረብ ፣ አገር ፣ የነበረውንና ፣ እስከ ፣ ሱዳን ፣ ያለውን ፣ የኢትዮጵያን ፣ ግዛትዋንና ፣ ሀብትዋን ፣ ወሰደባት ። በሰሜንም ፣ በኩል ፣ እንዲሁ ፣ አጕደለባት ። የሚያስፈራው ፣ ከባዱው ፣ ሰይፉ ፣ ግን ፣ አልደረሰባትም ። በተራራ ፣ የታጠረች ፣ ኢትዮጵያ ፣ በክርስቲያን ፣ ጥበቃ ፣ ዳነች ።

፪ ፤ አጼ ፣ ዐምደ ፣ ጽዮን ፣ በነገሡ ፣ በ፯ ፣ ዓ. ም. በሺ ፣ ፫፻፪ ፣ ዓ. ም. ከብዙ ፣ ትዕግሥት ፣ በኋላ ፣ ከረሺት ፣ የሚባሉ ፣ የእስላም ፣ ሕዝብ ፣ ዐሚሮች ፣ እየሆኑ ፣ ከዐረብ ፣ አገር ፣ ተነሥተው ፣ መጥተው ፣ ከሐበሻ ፣ ፣ ንጉሥ ፣ በታች ፣ ሆነን ፣ እንገብራለን ፣ እያሉ ፣ የባሕሩን ፣ ወደብ ፣ ዳርዳሩን ፣ ይይዙ ፣ ጀመር ። እንዲህም ፣ ማለታቸው ፣ እስኪበረቱ ፣ ድረስ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ ቃላቸው ፣ እውነት ፣ አልነበረም ። የመጡትም ፣ ዱዋሮን ፤ ታሪሂን ፤ ገድኤትን ፤ አደልን ፣ ይፋትን ፤ ባሌን ፤ ደራን ፣ ሌላም ፣ አገር ፣ ያዙ ።

፫ ፤ የኢትዮጵያ ፣ ነገሥታት ፣ በቸልተኝነት ፣ በመታለል ፣ ችላ ፣ ሳይሉዋቸው ፤ ገና ፣ ሳይጠነክሩ ፣ ቢወጉዋቸው ፣ ኑሮ ፣ በኋላ ፣ ጠላት ፣ አይሆኑዋቸውም ፣ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሁከትና ፡ ሽብር ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፤ ይህ ፡ ለእስላሞች ፡ በጣም ፡ ጠቀማቸው ።

፬ ፤ በይፋት ፡ ያሉ ፡ እስላሞች ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ናቸው ። አርጎባ ፤ ዶባ ፤ ሻጉራ ፤ ቃጭኖ ፡ የዓሊ ፡ ገዳዮች ፡ ናቸው ። ዓሊ ፡ የሙሐመድ ፡ አማች ፡ የፋጢማ ፡ የልጁ ፡ ባል ፡ ነው ።

፭ ፤ የእስላሞች ፡ መጀመሪያ ፡ ንጉሥና ፡ ነቢይ ፡ ሙሐመድ ፡ በመዲና ፡ ነገሠ ። መዲና ፡ ማለት ፡ በግእዝና ፡ በዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ከተማ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሙሐመድ ፡ ፷፫ ፡ ዓመት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሞተና ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ አበጋዝ ፡ ዐሚር፡አቡ በከር ፡ ሰዲቅ ፡ ከሊፋ ፡ ሆነ ፤ ማለት ፡ ነገሠ ። ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ፪ ፡ ዓመት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ ነው ። ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ዑመር ፡ ዕብነ ፡ አልሐጣብ ፡ ከሊፋ ፡ ሆነና ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ ምስርን ፡ ያዘ ። ፲ ፡ ዓመት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሞተና ፡ ኡስማን ፡ ዕብነ ፡ ሐሩን ፡ ከሊፋ ፡ ሆኖ ፡ እስክንድርያን ፡ ያዘ ። የኢትዮጵያ ፡ አገሮች ፡ መርዌ፡ በለውና ፡ ከለው ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ ሰለሙ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ አገር ፡ አስልሞ ፡ በነገሠ ፡ በ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ሞተና ፡ የፋጢማ ፡ ባል ፡ ዓሊ ፡ ነገሠ ። በነሱ ፡ ቍጥር ፡ በ፴፩ ፡ ዓመት ፡ ይኸው ፡ ዓሊ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ከነኸርዋን ፤ ኸዋርጅን ፡ የሚባሉ ፡ ከእስላሞች ፡ የማይጋጠሙ ፡ ሽፍቶች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ዓሊ ፡ ፈጃቸው ። ከ፬ሺ ፡ ሰዎች ፡ ፫ ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጡ ፡ ሁሉንም ፡ አረዳቸው ። ከነኸረዋን ፡ ቀጣሚት ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ከኸዋርጆዋን ፡ ውስጥ ፡ ስለነበሩ ፡ አባትዋ ንና ፡ ወንድሞችዋን ፡ ባልዋንም ፡ ዓሊ ፡ ፈጃቸው ።

፮ ፤ እኒህ ፡ ከዓሊ ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጡ ፡ ሰዎች ፡ እናግባሽ ፡ ቢልዋት ፡ እኔን ፡ የሚያገባ ፡ ዓሊንና ፡ መዓውያን ፡ አልአስን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ የገደለ ፡ ነው ። ያለዚያ፡ወንድ፡አለ ፡ ብዬ ፡ አላገባም ፡ ብትላቸው ፤ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ ሦስቱን፡ለመ ግደል ፡ በዕጣ ፡ ተካፈሉ ። አንዱ ፡ ወደ ፡ መዓውያ ፡ ሄደና ፡ መዓውያ ፡ ረጅም ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሳይገድለው ፡ ጕልበቱን ፡ ብቻ ፡ እንዳቆሰለው ፡ ተያዘና ፡ ተደብድቦ ፡ ሞተ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የቆሰለው ፡ ከጕልበቱ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ሆነ ፡ ጕልበቱ ፡ ደከሞአልና ፡ አልወለደም ። ይህ ፡ መዓውያ ፡ የሙሐመድ ፡ ታላቁ ፡ አበጋዝ ፡ ነው ።

፯ ፤ ወደ ፡ አልአስ ፡ የሄደው ፡ አሳስቶ ፡ ምስለኔውን ፡ ገደለና ፡ ተይዞ ፡ በምስር ፡ ከተማ ፡ በካይሮ ፡ ተሰቀለ ። ዕብነ ፡ አልአስም ፡ የሙሐመድ ፡ ታላቅ ፡ አበጋዝ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ምስርን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ ነው ።

፰ ፤ ወደ ፡ ዓሊ ፡ የሄደው ፡ በመስጊድ ፡ መንገድ ፡ ተሸምቆ ፡ (አድፍጦ ፡) ቈየ ውና ፡ በመርዛም ፡ ጦር ፡ ወጋውና ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ ሞተ ። ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ፩ ዓመት ፡ ከ፱ ፡ ወር ፡ ነው ። የገዳዩም ፡ ስም ፡ አብድረሁማን ፡ ይባል ፡ ነበር ። እር ሱም ፡ ተይዞ ፡ ተሰቀለ ።

፱ ፤ በይፋት ፡ ያሉ ፡ አርጎቦች ፤ የዚህ ፡ የዓሊ ፡ ገዳይ ፡ የአብዱረሁማን ፡ ዘሮች፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ ለመኖር ፡ የማይቻለቸው ፡ ሆነ ።

፲ ፤ ዓሊ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከፋጢማ ፡ የተወለደውን ፡ ልጁን ፡ ሐሰንን ፡ አነገሡት ። ሐሰን ፡ ግን ፡ እኔንም ፡ ልትገድሉኝ ፡ ነውን ፡ ብሎ ፡ አልነግሥም ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ ከሊፋነትን ፡ ማለት ፡ አልጋን ፡ በሻም ፡ አበጋዝ ፡ ለነበረው ፡ ለመዓውያ ፡ ሰጡትና ፡ ከሊፋ ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ የአብዱረህማን ፡ ልጆች ፡ የዓሊን ፡ ደም ፡ በቀል ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ በይፋት ፡ መጡ ፡ ማለት ፡ በግልጥ ፡ ይፋት ፡ ማለት ፡ ግልጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ እስላሞች ፡ በዐረብ ፡ እስላሞች ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ እስላም ፡ አይቈጠሩም ። ስማቸው ፡ ወይም ፡ አበጋዛቸው ፤ ወላስማ ፡ ይባላሉ ። ወላስማ ፡ ማለት ፡ ወላ ፡ እስላም ፡ ማለት ፡ ነው ። ወላ ፡ እስላም ፡ ማለትም ፡ እስላም ፡ ያይደለ ፡ ማለት ፡ ነው ። አባታቸው ፡ ዓሊን ፡ ስለ ፡ ገደለ ፡ ይህን ፡ ስም ፡ የተቀበሉት ፡ ከዐረቦች ፡ ነው ፡ ይባላል ። መልካቸው ፡ ዐረቦችን ፡ ይመስላሉ ። ቀዮች ፡ ናቸው ። ቋንቋቸውም ፡ ዐረብኛ ፡ ነው ። ግእዝን ፡ ይመስላል ። መጀመሪያ ፡ በሐበሻ ፡ የገቡ ፡ እስላሞች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ጥንት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ የኢትዮጲስ ፡ ልጆች ፤ ሳባ ፤ ኖባ ፤ በለው ፤ ከለው ፡ ናቸው ፤ በትግሬ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ የሳባ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

፲፩ ፤ የበለው ፡ ልጆች ፡ በድሆና ፡ በሐርንጎ ፡ በምጥዋ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። አለቃቸው ፡ ናይብ ፡ ይባላል ። የሰለሙትም ፡ በዓሊ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፲፪ ፤ የኖባ ፡ አገር ፡ ከአትባራና ፡ ከተከዚ ፡ በመለስ ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ ወንጌላዊ ፡ አጥምቋቸው ፡ ክርስቲያን ፡ ሁነው ፡ ነበሩ ። በዓሊ ፡ ጊዜ ፡ ሰለሙ ፤ ከተማቸው ፡ ካርቱም ፡ ነው ።

፲፫ ፤ በኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ እስላሞች ፡ አራት ፡ ዐይነት ፡ ናቸው ። መጀመሪያ ፡ ሕምርያ ፤ ወይም ፡ ሕምያር ፡ ይባላሉ ። ቀይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ ትግሬ ፡ ይባላሉ ። ነጋዴ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፫ኛ ፡ አርጎቦች ፡ ናቸው ። ፬ኛ ፡ በመዓውያን ፡ ጊዜ ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተሰደው ፡ የመጡት ፡ ናቸው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የእስላሞች ፡ ንጉሥና ፡ ነቢይ ፡ ሙሐመድ ፡ የተነሣው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ? አገሩስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ እስላሞች ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ተነሥተው ፡ የመጡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? በማን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ ? በኋላ ፡ እነማን ፡ የሚባሉትን ፡ አገሮች ፡ ያዙ ፡ ?

፫ ፤ በኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ እስላሞች ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ናቸው ።

## ም ስ ራ ፍ ፰ ።

### ነገደ ፡ ወረሴህ ።

፩ ፤ የወረሴህ ፡ ታሪክና ፡ ትውልድ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ግራኝ ፡ አሕመድ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፡ በሺ ፡ ፲፭፻፲፱ ፡ ዓ. ም. ከባሕር ፡ ማዶ ከዐረብ አገር ፡ ሼህ ፡ ዑመር ፡ የሚባል ፡ የብር ፡ ዘንግ ፤ የብር ፡ ርኮት ፤ አስይዞ ፡ መጣና ፡ በየጁ ፡ ገብቶ ፡ ተቀ

መጠ ፣ ሼህ ፡ ዑመር ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ አግብቶ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወለደና ፡ መን
ደሩ ፡ ቢባዛ ፡ ወረሺህ ፡ ተባለ ። አሁን ፡ ወረሴህ ፡ የሚባሉ ፡ የሱ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ።
ወረሺህ ፡ ማለት ፡ የሺህ ፡ መንደር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ልጆቹ ፡ ከወረሺህ ፡ ወረ
ሴህ የመባል ስም ፡ ተቀበሉ ።
፪ ፣ ከሼህ ፡ ዑመር ፡ ልጆች ፡ የበኵሩ ፡ ወሌ ፡ ይባል ፡ ነበር ፣ ወሌ ፡ አብዬን ፡
ወለደ ፣ አብዬ ፡ ቢወልድ ፡ በአባቱ ፡ ስም ፡ ወሌ ፡ አለው ፣ ወሌ ፡ አባ ፡ ገትየን ፡
ወለደ ፣ አባ ፡ ገትየ ፡ አባ ፡ ሴሩ ፡ ጓንጉልን ፡ ወለደ ።
፫ ፣ አባ ፡ ሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ መልኩ ፡ እጅግ ፡ ያማረና ፡ የተዋበ ፡ ነበር ። ኃይለኛ ፡
ጀግና ፡ ፈረሰኛ ፡ ሆነ ። ጀግንነቱና ፡ ኃይለኝነቱ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ የታወቀ ፡
ሆነ ። ክርስትና ፡ ተነሣና ፡ የላስታንና ፡ የሰለዋን ፡ ባላባት ፣ የራስ ፡ ፋሪስን ፡ እት ፡
ወይዘሮ ፡ ገለቡን ፡ አግብቶ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፣ የሱም ፡ ዘር ፡ ሲወርድ ፡
ሲዋረድ ፡ ብዙ ፡ ትውልድ ፡ ሆነ ።
፬ ፣ እኒህ ፡ ወረሴሆች ፡ የጓንጉል ፡ ልጆች ፡ ከታላቅ ፡ ዓሊ ፡ እስከ ፡ ታናሽ ፡ ዓሊ ፡
በክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ከነየልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ፲ ፡ መሳፍንት ፡ የጁን ፣
ላስታን ፣ አገውን ፣ ዋድላን ፣ ደላንታን ፣ ወሎን ፣ በጌምድርን ፣ ስሜንን ፣ ጎን
ደርን ፡ ወገራን ፣ ደምቢያን ፣ ቋራን ፣ አገው ፡ ምድርን ፣ ዳሞትን ፣ ጐጃምን ፡
አንድ ፡ አድርገው ፣ የጎንደርን ፡ መንግሥት ፡ አጥፍተው ፣ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ገዙ ።
፭ ፣ እኒህ ፡ ወረሴሆች ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑት ፡ በጓንጉል ፡
ጊዜ ፡ ነው ። ልጆቹ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሆነው ፡ ታላቁ ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ ባገራቸው ፡
በየጁ ፡ ፲ ፡ ደብሮች ፡ ተከለዋል ። አድባራቱም ፡ ጉባርጃ ፡ ማርያም ፣ ጉባላፍቶ ፡
አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፣ ወልያ ፡ ገብርኤል ፣ ኪቢቃሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፣
ዘምል ፡ ጊዮርጊስ ፣ ገዶ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፣ ሾዋና ፡ ማርያም ፡ ናቸው ።
፮ ፣ የጁ ፡ ጥንተ ፡ ስምዋ ፡ ገነቴ ፡ ትባል ፡ ነበር ። ጉባርጃ ፣ ማርያም ፡ በገነቴ ፡
ምድር ፡ የከበረች ፡ ደብር ፡ ናት ፣ ብዙ ፡ ጳጳሳት ፡ ይኖሩባት ፡ ነበር ። ፲ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ ተቀብረውባታል ፡ ይባላል ።
፯ ፣ የጁ ፡ የተባለችበት ፡ ምክንያት ፡ እንዲህ ፡ ነው ። በዚህች ፡ አገር ፡ በጣዖት ፡
የሚያመልኩ ፡ በአስማታቸው ፡ የሚመኩ ፣ አስማተኞች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። በዚያ ፡
ዘመን ፡ የነበረ ፡ ጳጳስ ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፣ በወንጌል ፡ እመኑ ፣ አስማት ፡ ማድረግን ፡
ጣዖት ፡ ማመለክን ፡ ተዉ ፡ ብሎ ፡ ቢገሥጻቸውና ፡ ቢመክራቸው ፡ እጅግ ፡ አጥ
ብቀው ፡ ጠሉት ፣ ቃሉንም ፡ አልተቀበሉትም ። ያለነዚህ ፡ አስማተኞች ፡ በቀር ፡
የቀሩት ፡ ታላላቆቹ ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ እየሄዱ ፡ የወንጌልን ፡ ትምህ
ርትና ፡ ሃይማኖት ፡ እየሰሙ ፡ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ ብዙዎቹ ፡ ወደ ፡ ክርስ
ትና ፡ ይገቡ ፡ ጀመር ። አስማተኞችም ፡ ክብራቸውን ፡ እንደ ፡ ተገፈፉ ፣ በሥራ
ቸው ፡ እንደ ፡ ተነቀፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ሰርቀው ፡ በሥውር ፡ አር
ደው ፡ ለጳጳሱ ፡ ወጥ ፡ ሠሪ ፣ ይህን ፡ ወጥ ፡ ሠርተህ ፡ ጳጳሱ ፡ ግብር ፡ በሚያበ

ላበት ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳሱ ፡ ፊት ፡ ይህን ፡ አቅርብልን ። ይህ ፡ ምንድነው ፡ ቢሉህ ፡
የወትሮ ፡ ግብርዎ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አሳፍርልኝ ፡ ብለው ፡
እጅግ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡት ። እርሱም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ እንዳሉት ፡
አደረገ ። የወጡ ፡ ሰታቴ ፡ ድስት ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ የዚያ ፡ ሕፃን ፡ ሁለቱ ፡ እጆቹ ፡
ከሌላው ፡ ሥጋው ፡ ጋር ፡ ወጥ ፡ ተሠርቶ ፡ አዩ ። ጳጳሱና ፡ አብሮ ፡ የተቀመጡ
ትም ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ አጥብቀው ፡ ደነገጡ ። አንተ ፡ ዛሬ ፡ ያደረግኸው ፡ ነገር ፡
ምንድር ፡ ነው ፡ ቢሉት ። እንደ ፡ ተመከረው ፡ ጌታዬ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡
አላመጣሁም ፡ ያው ፡ የወትሮው ፡ ግብርዎ ፡ ነው ፡ አላቸው ። ሰዎቹም ፡ ሁሉ ፡
እጅግ ፡ ደነገጡ ። ጳጳሱም ፡ እጅግ ፡ አዘኑና ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ የሰው ፡
ሥጋ ፡ ስበላ ፡ ታውቀኛለህን ፡ ? አንተ ፡ ከጠላቶቼ ፡ በገንዘብ ፡ ተገዝተህ ፡ በገ
ንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ልብህ ፡ ጠፍቶ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ድፍረትና ፡ ክፋት ፡ አድርገሃ
ልና ፡ ለዘለዓለም ፡ ርጉም ፡ ሁን ፤ እንቡዘ ፡ ልብ ፡ ሁን ፡ ብለው ፡ ቢረግሙት ፡
ያን ፡ ጊዜውን ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፤ ሱሪውን ፡ ቀዶ ፤ ራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ በሰዎቹ ፡
ፊት ፡ እብዶ ፡ በረረና ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ሞተ ። ይህንን ፡ ያዩ ፡ ብዙዎቹ ፡ ከነ
ዚያ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ገቡ ። አገሩንም ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የኔን ፡
ስም ፡ ለማክፋት ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ገድሎ ፡ እጁን ፡ ቈርጦ ፡ አናቱን ፡ ፈጥፍጦ ፡
በሰው ፡ እንደ ፡ ተጫወተ ፡ የጁን ፡ ይስጠው ፤ ሁልጊዜ ፡ ደም ፡ ይፍሰስበት ፡ ርስ
በርሱ ፡ ይተላለቅበት ፤ ጳጳስም ፡ አይቀመጥበት ፡ ብለው ፡ ረገሙት ። ከዚያ ፡
ወዲህ ፡ አገሩ ፡ ገነቴ ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ የጁ ፡ ተባለ ። እርስ ፡ በርሱም ፡ በወፋ ፡
ውጊያ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሰው ፡ ደም ፡ የሚፈስበት ፤ በከንቱ ፡ ነፍስ ፡ የሚወድቅበት ፡
የተረገመ ፡ አገር ፡ ሆነ ።

፰ ፤ የየጁ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ መርገም ፡ ስለ ፡ ጸናባቸው ፡ አገር ፡ ላትገዙበት ፤ ጠጅ ፡
ላትጠጡበት ፤ ቀሚስ ፡ ላትለብሱበት ፤ ስም ፡ ላታወጡበት ፤ ስለምን ፡ ርስ ፡ በር
ሳችሁ ፡ ትጋደላላችሁ ፡ ? ቢሉዋቸው ፡ ቆሌዬቱ ፡ ደም ፡ ትወዳለችና ፡ ወፋ ፡
ውጊያ ፡ ሲቀር ፡ ከአፋፍ ፡ ላይ ፡ ዘልቃ ፡ እርሪ ፡ ትላለች ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ከያገሩ ፤ ይወጣና ፡ በየመልካው ፡ ይወርዳል ። በይላ ፡ ወንዝ ፤
በጥቍር ፡ ውሃ ፤ በሸሊ ፤ በሚሌ ፤ እየወረደ ፡ ወፋ ፡ ይዋጋል ፡ ይላሉ ። ይህስ ፡
ቢሆን ፡ ክርስቲያን ፡ ከሆናችሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ካመናችሁ ፡ ይህን ፡ ከንቱ ፡ የሆነ ፡
ክፉ ፡ ሥራ ፡ ብትተዉት ፡ ምነው ፡ ቢሉዋቸው ፡ ያገሩ ፡ ቆሌ ፡ የሰው ፡ ደም ፡
የለመደች ፡ ናትና ፡ ወፋ ፡ ውጊያ ፡ ሲቀር ፡ ከሰማይ ፡ ዝናብ ፡ ያንስብናል ፤ ብናር
ስም ፡ እህሉ ፡ ይጠፋብናል ፤ አገራችንም ፡ ይራብብናል ፤ በሽታም ፡ ይነሣብናል ፤
ወፋ ፡ በተዋጋን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዝናም ፡ በበረከት ፡ ይወርድልናል ፤ እህልም ፡ ይሆ
ናል ፡ አገራችንም ፡ ጥጋብና ፡ ጤና ፡ ይሆናል ፡ ይላሉ ።

፱ ፤ ባጠገባቸውና ፡ በዙሪያቸውም ፡ ያሉት ፡ ጐረቤቶቻቸው ፡ አረማውያኑና ፡ በስም ፡

ክርስቲያን ፣ የሚባሉትም ፣ ሳይቀሩ ፣ ይህን ፣ ከንቱ ፣ ወሬ ፣ እየሰሙ ፣ ባገራቸው ፣ ዝናምና ፣ በረከት ፣ የእህል ፣ ብዛትና ፣ ጤናም ፣ እንዲሆን ፣ አስበው ፣ ይህን ፣ ወፉ ፣ ውጊያ ፣ ለመዱ ።

፲ ፤ ይህም ፣ ወፉ ፣ ውጊያ ፣ እስከ ፣ ሸዋ ፣ ድንበር ፣ እስከ ፣ ዶባና ፣ እስከ ፣ መርሐ ፣ ቤቴ ፣ ተለምዶ ፣ እስከ ፣ ዳግማዊ ፣ ምኒልክ ፣ ዘመን ፣ ድረስ ፣ ይዋጉ ፣ ነበሩ ። ጃንሆይ ፣ አጼ ፣ ምኒልክ ፣ ይህን ፣ ወፉ ፣ የተባለውን ፣ ከንቱ ፣ ጥፋት ፣ ባዋጅ ፣ አስተውት ። ብዙ ፣ ቀንም ፣ በሥውር ፣ ተጣቅሶ ፣ ወርዶ ፣ ርስበርሱ ፣ እየተዋጋ ፣ እስቸግሮ ፣ ስለ ፣ ነበር ፣ በገዳይና ፣ በሙዋች ፣ ቤት ፣ ዕዳ ፣ እያስከፈሉ ፣ አስተውት ፤ ይህም ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ በማመስገን ፣ ፈንታ ፣ ይህን ፣ በከንቱ ፣ መሞት ፣ አስቀሩብን ፣ ብሎ ፣ ያዝናል ። ልብ ፣ ያለውና ፣ ያስተዋለ ፣ ግን ፣ በወፉ ፣ ውጊያ ፣ መቅረት ፣ እግዚአብሔርንና ፣ ጃንሆይን ፣ ያመሰግናል ። ባለፈውም ፣ በዘመዶቹ ፣ ከንቱ ፤ ጥፋት ፣ ይጸጸታል ።

## ጥያቄ ።

የወረሴሆች ፣ አባት ፣ ማን ፣ ይባላል ፣ ? ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገባው ፤ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? የመጣውስ ፣ ከየት ፣ ነው ፣ ?

ወረሴህ ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ?

፩ ፤ የሼህ ፣ ዑመር ፣ ልጆች ፣ ማንና ፣ ማን ፤ ይባላሉ ፣ ? ትውልዳቸውን ፣ ዘርዝረህ ፣ ተናገር ።

፪ ፤ ወረሴህ ፣ ሃይማኖታቸው ፣ ምን ፣ ኖርዋል ፣ ? የወረሴህ ፣ መሳፍንት ፣ ስንት ፣ ኖረዋል ? ማንና ፣ ማን ፣ የተባሉትን ፣ አገሮች ፣ ይገዙ ፣ ኑረዋል ፣ ?

፫ ፤ እነዚህ ፣ ወረሴሆች ፣ ክርስትናን ፣ የተቀበሉት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?

፬ ፤ የጁ ፣ ጥንት ፣ ስምዋ ፣ ማን ፣ ኑሮዋል ፣ ?

፭ ፤ በዚያን ፣ ዘመን ፣ ስለ ፣ ነበረው ፣ ጳጳስና ፣ ስለ ፣ ሕዝቡ ፣ ዘርዝረህ ፣ ተናገር ።

፮ ፤ ስለ ፣ የጁ ፣ ሕዝብ ፣ ልማድ ፣ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፣ ፳፩ ።

### ነገደ ፣ ጉራጌ ።

፩ ፤ የነገደ ፣ ጉራጌ ፣ ነገር ፣ እንዲህ ፣ ነው ። ባአጼ ፣ ዐምደ ፣ ጽዮን ፣ ዘመን ፣ ከትግሬ ፣ ጉርዓ ፣ ከሚባል ፣ አገር ፣ ከኰሎ ፣ ግዛይ ፣ ክፍል ፣ የወጣ ፣ ሠራዊት ፣ ከአዝማች ፣ ስብሐት ፣ ጋር መጥቶ ፣ በአይመለል ፣ ተሠራ ። ስለዚህ ፣ ያ ፣ አገርና ሕዝብ ፣ ጉርዓጌ ፣ ይባላል ። አጼ ፣ ዐምደ ፣ ጽዮን ፣ የነገሡት ፣ ካንድ ፣ ሺ ፣ ፫፻፳፯—፩ሺ ፫፻፵፫ ፣ ዓ . ም . ነው ፤ ዘመነ ፣ መንግሥታቸው ፣ ፴ ፣ ዓመት ፣ ነው ።

፪ ፤ የጉርዓጌ ፣ ሕዝብ ፣ ከጉርዓ ፣ ተነሥተው ፣ ወደ ፣ አይመለል ፣ የገቡ ፣ በዚያ ፣ ዘመን ፣ ነው ። ጉርዓጌ ፣ ማለት ፣ የጉርዓ ፣ ሰዎች ፣ ምድር ፣ ወይም ፣ አገር ፣ ማለት ፣ ነው ።

ዳግመኛም ፡ ከንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ ግራ ፡ ስለ ፡ ሰፈሩ ፡ ግራጌ ፡ ተባሉ ። በቀን ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ ግራጌ ፡ ተለውጦ ፡ ጉራጌ ፡ ተባሉ ።

## ጥያቄ ።

ነገዱ ፡ ጉራጌ ፡ ጥንተ ፡ ነገዱ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከአገሩ ፡ የወጣው ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ? አስቀድሞ ፡ የገባው ፡ በየትኛው ፡ አገር ፡ ነው ፡ ? ይህ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? በማን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ ? ጉርዓጌ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

### ከምጥዋ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ በቆላው ፡ ስላሉ ፡ ሕዝብ ።

፩ ፤ ከምጥዋ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ቋራ ፡ ጥግ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ልዩ ልዩ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ። በፊት ፡ እንዳሳየን ፡ የሳባ ፡ ልጆች ፡ በትግሬ ፡ ይኖራሉ ። እኒህ ፡ የኢትዮጲስ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ የተለዩ ፡ የበለው ፡ ልጆች ፡ በዶሆና ፡ በሐረርጊጎ ፤ በምጥዋ ፡ በምንኩሉ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፤ አለቃቸው ፡ ናይብ ፡ ይባላል ።

፪ ፤ ከለው ፡ ከሳባ ፡ ወደ ፡ ምዕራብና ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ያለ ፡ ፀአማራ ፤ በወልቃይት ፤ በጠገዴ ፡ በጠለምት ፡ በአርማጭሆ ፡ በዳዋ ፡ በቋራ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ አባት ፡ ነው ።

፫ ፡ የኖባ ፡ ልጆች ፡ ደግለሎች ፡ ጓሊሎች ፡ ምንዐሚሮች ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ በቆላው ፡ የሚኖሩ ፡ ኩናሞች ፡ ሱዳኖች ፡ ትክሬሮች ፡ ግንጃሮች ፡ ፌግኖች ፡ ሻንቅሎች ፡ የካም ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ከበለው ፡ ገለባትና ፡ የባርያ ፡ ሻጭ ፡ (ሻግያ) ፡ ባለመከራ ፡ የሚባሉ ፡ ወገን ፡ አሉ ። ለምልክት ፡ ገላቸውን ፡ ይበጣሉ ። ከአዲያቦ ፡ በስተሰሜን ፤ ባርያ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ ሕዝብ ፡ አሉ ። ከነርሱ ፡ መኻከልም ፡ ኢልግ ፡ የሚባሉ ፡ ጨዋዎች ፡ አሉ ። የሰውነታቸው ፡ መልክ ፡ ሁሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በምንም ፡ አይለዩም ። የብቻቸው ፡ ቋንቋና ፡ ፊደል ፡ መጻሕፍትም ፡ አሏቸው ፡ ይላሉ ፡ ከወገናቸው ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ እንዳያውቅባቸው ፡ እነዚያን ፡ መጻሕፍቶቻቸውን ፡ በብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ ይጠብቁዋቸዋል ። ይህ ፡ ትምህርት ፡ በምሥጢር ፡ ከአባት ፡ ወደልጅ ፡ እየተያያዘ ፡ ይወርዳል ። ከነሱም ፡ የሚማሩት ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በምድር ውስጥ ፡ እንደ ፡ አዳራሽ ፡ የሆኑ ፡ እጅግ ፡ ሰፋፊ ፡ ዋሻዎች ፡ አሉዋቸው ። በድንገት ፡ በሜዳ ፡ ሳሉ ፡ አደጋ ፡ ካልጣሉባቸው ፡ ጠላት ፡ ሊያገኛቸው ፡ አይችልም ። አምልኮዋቸው ፡ ከክርስቲያንና ፡ ከእስላም የተለየ ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ከምጥዋ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ቋራ ፡ ጥግ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ የማን ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ?

፬ ፤ ከነዚህም ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፡ ልዩ ፡ ልማድና ፡ ቋንቋ ፤ ፊደልና ፡ መጻሕፍትም ፡ ያሉዋቸውን ፤ ሃይማኖታቸውንና ፡ አምልኮታቸውን ፤ መኖሪያቸውንም ፡ ጭምር ፡ ዘርዝረህ ፡ አስረዳ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳፫ ።

### ከሐረርጌ ፡ እስከ ፡ ምጥዋ ፡ ወሰን ፡ ስላሉ ሕዝብ ።

፩ ፤ ከሐረርጌ ፡ እስከ ፡ ምጥዋ ፡ ወሰን ፡ ቆላ ፡ ቆላውንና ፡ በረሃውን ፡ የያዙ ፡ ሕዝብ ፡ በፊት ፡ ከዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ነገደ ፡ አባልና ፡ ነገደ ፡ አፊር ፡ ነበሩ ። ነገደ ፡ አባል ፡ የአዳልንና ፡ የሱማሌን ፡ ምድር ፤ ነገደ ፡ አፊር ፡ የኢሳንና ፡ የውጋዴን ፡ ምድር ፡ ይዘው ፡ ነበር ። የነገደ ፡ አፊር ፡ ከተማ ፡ በውጋዴን ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ ፡ ኮፊር ፡ የሚባለው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ነገደ ፡ ኢሳ ፤ ነገደ ፡ ሱማሌ ፤ ነገደ ፡ አዳል ፤ ነገደ ፡ ዳንከሊ ፤ ነገደ ፡ ሻሆ ፤ ነገደ ፡ ቶርን ፡ ነገደ ፡ አሳሁርታ ፤ ነገደ ፡ ጥልጣል ፡ ከእስያ ፡ መጥተው ፡ ነገደ ፡ አባልን ፡ አስለቅቀው ፡ አገሩን ፡ ወረሱ ። ነገደ ፡ ሱማሌ ፤ ነገደ ፡ ኢሳ ፤ የአፊርን ፡ ሕዝብ ፡ አስለቅቀው ፡ አገሩን ፡ ወረሱ ። ነገደ ፡ አባልና ፡ ነገደ ፡ አፊር ፡ ከዚያ ፡ ተሰደው ፡ ወደ ፡ ደጋው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጥተው ፡ ከነገደ ፡ ሳባ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ተቀላቀሉ ። የጥንት ፡ አገራችንን ፤ አንለቅም ፡ ያሉትና ፡ ለመሰደድ ፡ ጕልበትና ፡ ኃይል ፡ ያጡት ፡ ግን ፡ ከነዚያ ፡ ተመሳስለው ፡ ቀሩና ፡ ሰለሙ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ በየጊዜው ፡ ከእስያ ፡ እየፈለሱ ፡ የገቡ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፪ ፤ ኢሳ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ የኤሳው ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ። አዳል ፤ ሱማሌ ፤ ዳንከሊ ፤ የካም ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ሻሆ ፤ ቶርን ፤ አሳሁርታ ፤ ጥልጣል ፤ ከዐረብ ፡ ዘር ፡ ናቸው ። ሻሆ ፤ ቶርን ፤ አሳሁርታ ፤ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተቀላቅለዋል ። አገራቸውም ፡ በቶርን ፡ ወይም ፡ በአሳሁርታ ፡ ስም ፡ ይጠራል ።

፫ ፤ አዳሎችና ፡ ጥልጣሎችም ፡ ስለተቀላቀሉ ፡ እንዲሁ ፡ ቋንቋቸው ፡ ይመሳሰላል ። ሁሉም ፡ የሰለሙት ፡ በዓሊ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡበት ፡ ጊዜና ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ አይታወቅም ።

### ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከሐረርጌ ፡ እስከ ፡ ምጥዋ ፡ ወሰን ፡ ቈላ ፡ ቈላውንና በረሃውን ፡ የያዙ ፡ ሕዝብ ፡ የማን ፡ ነገድ ፡ ናቸው ፡ ?
ማንና ፡ ማን ፡ የተባሉትን ፡ ምድሮች ፡ ይዘው ፡ ኑረዋል ፡ ? የነገደ ፡ አፊር ከተማ ፡ ማን ፡ ይባል ፡ ኑሮዋል ፡ ?
በማንኛው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ኖሮዋል ፡ ? ዛሬ ፡ አገሩን ፡ ወርሰው ፡ የሚኖሩበት ፡ ነገድ ፡ ማንና ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ? እነዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ከየት ፡ የመጡ ናቸው ፡ ?

፱ ፤ ኢሳ ፡ የተባሉ ፡ ሕዝብ ፡ የማን ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ። አዳል ፤ ሱማሌ ፤ ዳንካሌስ ፤ ? ሻሆ ፤ ቶርን ፤ አሳሁርታ ፤ ጥልጣልስ ፡ ?

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳፬ ።

### የሐረርጌ ፡ ሕዝብ ።

፩ ፤ ከሐረርጌ ፡ ግንብ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ከሐማሴን ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። በአጼ ፡ ዳዊት ፡ ዘመን ፡ በሐማሴን ፡ አንድ ፡ ኃይለኛና ፡ ጀግና ፡ ሰው ፡ ነበር ። በኃይለኛ ነቱ ፡ ሰው ፡ ስለጠላው ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ለብቻው ፡ በችፍግ ፡ ዱር ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ተቀመጠ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሚስቱ ፡ ብዙ ፡ ቅቤ ፡ ስላጠጣችው ፡ ደክሞት ፡ ከቤቱ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ሚስቱ ፡ ግን ፡ ልጆችዋን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስባ ፡ ይዛ ፡ አዝመራ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ሄዳ ፡ ውላ ፡ ማታ ፡ ከልጆችዋ ፡ ጋር ፡ ብትመለስ ፡ ባልዋን ፡ አንበሳ ፡ ጐትቶ ፡ ገድሎት ፡ ሳይበላው ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡ ተንዘራግቶ ፡ ቈያት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሆዱን ፡ ቀዳ ፡ የጠጣውን ፡ ቅቤ ፡ ከሆዱ ፡ ቀድታ ፡ ለወንዶቹ ፡ ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ አቀመሰቻቸው ። ይህንንም ፡ ማድረጉዋ ፤ ጠንቋይ ፡ ባልሽ ፡ ሊሞት ፡ ጊዜው ፡ ደርሶዋል ። በድንገት ፡ ሳይታሰብ ፡ አንበሳ ፡ ይገድለዋል ፤ የሚሞተውም ፡ ቅቤ ፡ የጠጣለት ፡ ስለ ሆነ ፡ አንበሳ ፡ ከገደለው ፡ በኋላ ፡ ሆዱን ፡ ቀደሽ ፡ ከሆዱ ፡ ያለውን ፡ ቅቤ ፡ በዕቃ ፡ ተቀብለሽ ፡ ለልጆችሽ ፡ አጠጪቻቸው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ባለግርማ ፡ ይሆናሉ ፤ ጠላትም ፡ ከፊታቸው ፡ አይቆምም ፤ አሸናፊዎችና ፡ የሚያስፈሩ ፡ ይሆናሉ ፡ ብሏት ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጠላቶች ፡ ያባታቸውን ፡ ሞት ፡ ሰምተው ፡ እንግዲህ ፡ የዚያን ፡ የርጉም ፡ ልጆች ፡ ከምድር ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለው ፡ ተነሡባቸው ። በተዋጉም ፡ ጊዜ ፡ እኒህ ፡ ልጆች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ፈጁዋቸው ። ጦርም ፡ ከፊታቸው ፡ የማይቆም ፡ ሆነ ። አገር ፡ እያሴረ ፡ እንደገና ፡ ጦር ፡ እየሆነ ፡ ቢያስቸግራቸው ፡ ኀዛቸውን ፤ አንሥተው ፤ ከብታቸውን ፡ ነድተው ፡ እየተዋጉና ፡ እየተከላከሉ ፡ እስከ ፡ ሐረርጌ ፡ ተሰደዱና ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ። ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዙሪያቸው ፡ ያለ ፡ ጋላ ፡ የማያኖራቸው ፡ ቢሆን ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ አንዱን ፡ በላያቸው ፡ አለቃ ፡ ሾመው ፡ ጋላውን ፡ እየተዋጉ ፡ ድል ፡ አደረጉና ፡ ገዙት ። ሌሊት ፡ አደጋ ፡ እየጣለ ፡ ቢያስቸግራቸው ፡ የአገራቸውን ፡ ዙሪያ ፡ በብርቱ ፡ ግንብ ፡ አጠሩትና ፡ ፭ ፡ በር ፡ አደረጉለት ። ቋንቋቸው ፡ ትግሪኛ ፡ የነበረው ፡ ከዘመን ፡ ብዛት ፡ ተለውጦ ፡ ሌላ ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸውም ፡ ቢሆን ፡ ከትግሪኛ ፡ ብዙ ፡ ይመሳሰላል ። በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሳትደክም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይገዙና ፡ ይገብሩ ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ለቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ተገዙ ።

፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባ፲፰፻፸፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጃንሆይ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ሐረ

ርጌን ፡ ከፍተው ፤ ንጉሡን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ያዙና ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ሹመው ፡ ተመለሱ ። የሐረርጌ ፡ ቋንቋ ፡ ከግንብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከውጪ ፡ የለም ።

፬ ፤ ይህ ፡ የተቈጠረው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ጥንት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዜጋ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከታላቅነትዋና ፡ ከስፋትዋ ፡ እያነሰችና ፡ እየጠበበች ፡ ሄዳ ችና ፡ ዛሬ ፡ የቀራት ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ፫ ፡ ክፍሎች ፡ ቆላ ፡ ደጋ ፤ ወይና ፡ ደጋ ፡ ይባላሉ ።

## ጥያቄ ።

ከሐረርጌ ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ከየት ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ ? ስለጀግናው ፡ ሐማሴንና ፡ ስለሚስቱ ፡ ስለ ፡ ልጆቹም ፡ ተናገር ። አገራቸውን ፡ በግንብ ፡ የከበቡት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ? የቀድሞ ፡ ቋንቋው ፡ ምን ፡ ኖሮዋል ፡ ?

በፊት ፡ ለማን ፡ መንግሥት ፡ ይገዙ ፡ ኑረዋል ፡ ? በኋላስ ፡ ?

፪ ፤ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ሐረርጌን ፡ የከፈቱት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ከመጀመሪያ ፡ እስከዚህ ፡ የተነገሩት ፡ አህጉርና ፡ ሕዝብ ፡ የማን ፡ መንግሥት ፡ ዜጋ ፡ ኑረዋል ? ፡ አሁንስ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ወሰንና ፡ በውስጥዋም ፡ ስለሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ።

፩ ፤ የጥንት ፡ ወሰኑዋ ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ማዳጋስካር ፤ በስተ ፡ ሰሜንና ፡ በስተ ፡ ምዕራብ ፡ እስከ ፡ ግብፅና ፡ እስከ ፡ ኖብያ ፡ ዳርቻ ፤ በስተ ፡ ደቡብ ፡ ዛሬ ፡ ቪክቶርያ ፡ ኒያንዛ ፡ እስከ ፡ ተባለው ፡ እስከ ፡ ኒያንዛ ፡ ባሕር ፡ ነበር ።

፪ ፤ በቆላው ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አትክልትና ፡ ፍሬ ፡ ይገኝበታል ። በደቡብ ፡ ቆላ ፡ በባሊ ፤ በቦረና ፤ በጅጅጋ ፡ አውራጃ ፡ የዕጣንና ፡ የላስቲክ ፡ ዛፍ ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨት ፤ ከርቤ ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ቅመምና ፡ የሚበላ ፡ ፍሬ ፡ ይገኝበታል ። የከበረ ፡ የጠራ ፡ ወርቅና ፡ ዕንቍ ፡ ሉልም ፤ ዝባድና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሽቱም ፡ ይገኝበታል ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ኃይሏ ፡ እየደከመ ፡ ፍቅርና ፡ አንድነት ፡ ዕውቀትም ፡ እያደረ ፡ ቢጐድልባት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አገሩዋን ፡ ሁሉ ፡ ከውጪ ፡ የመጡ ፡ ባዕዳን ፡ ሕዝብ ፡ ያዙባት ።

፫ ፤ ጥበብንም ፡ ከብልሃተኞች ፡ መጠየቅን ፡ ናቀችና ፡ ችላ ፡ ስለ ፡ አለች ፡ ከቀድሞው ፡ ዕውቀቷ ፡ እጅግ ፡ በረደችና ፡ ቀዘቀዘች ፤ በጣምም ፡ አነሰች ።

፬ ፤ ፬፻፳፬ ፡ ዓመት ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ሄሮዱቱስ ፡ የተባለ ፡ ዕርዓዊ ፡ ከርሱ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ምስርን ፡ ጨምረው ፡ የገዙትን ፡ የኢትዮጵያን ፡

ነገሥታት ፣ ሲጽፍ ፣ ፲፰ ፣ ነገሥታት ፣ ምስርን ፣ ጨምረው ፣ ገዝተዋል ፣ ሲል ፣ በታሪክ ፣ መጽሐፉ ፣ ጽፎዋል ።

፭ ፤ ደግሞም ፣ ይኸው ፣ ሄሮዱቱስ ፣ ስለ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ ደግነት ፣ ሲናገር ፣ በኢትዮጵያ ፣ እጅግ ፣ ያማሩና ፣ ባለደም ፣ ግባት ፣ ቆንጆዎችና ፣ ውቦች ፣ ሰዎች ፣ አሉባት ። ርኅራኄያቸውም ፣ እንደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ነው ። በመንገድ ፣ ለሚያልፍ ፣ ሰው ፣ የሚሆን ፣ ድግስ ፣ ያሰናዳሉ ። ምንም ፣ ቢሆን ፣ መንገደኛ ፣ የሚበላውን ፣ አያጣም ። ዕድሜያቸው ከመቶ ፣ እስከ ፣ መቶ ፣ ኻያ ፣ እስከ ፣ መቶ ፣ ሠላሳም ፣ ይኖራሉ ። ነውርና ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ በአገራቸው ፣ የተጠላ ፣ ነው ። የጤና ፣ ምንጮች ፣ የሚሆኑ ፣ ውሆች ፣ ስላሉዋቸው ፣ በጠጡዋቸው ፣ ጊዜ ፣ ሰውነታቸው ፣ ይታደሳል ። በሀብትም ፣ እጅግ ፣ ባለጠጎች ፣ ናቸው ።

፮ ፤ እንዲህ ፣ ያለች ፣ እጅግ ፣ ያማረች ፣ በልዩ ፣ ወገን ፣ ሰውና ፣ በባዕድ ፣ አፍ ፣ የተመሰገነች ፣ ክብርት ፣ የነበረች ፣ አገር ፣ ዛሬ ፣ ፍቅር ፣ በማጣት ፣ እርስ ፣ በርሱዋ ፣ ባለመስማማት ፣ የአንድነት ፣ ኃይልዋን ፣ አፍርሳ ፣ በመለያየት ፤ የደም ፣ መፍሰስ ፣ የግፍ ፣ የክፋት ፣ የነውር ፣ ሁሉ ፣ ከተማ ፣ ሆነች ።

፯ ፤ የኢትዮጵያ ፣ ቆላ ፣ ሙቀት ፣ ያመቱን ፣ ሙቀት ፣ ሲያካፍሉት ፣ ከ፳—፳፭ ፣ ዴግሬ ፣ (ማዕርግ ፣ ) ይደርሳል ።

፰ ፤ ወይና ፣ ደጋው ፣ እጅግ ፣ ጤናማ ፣ አገር ፣ የሰጡትን ፣ ዘርና ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ አትክልትም ፣ የሚያበቅል ፣ ነው ። ሙቀቱም ፣ በዓመት ፣ ቢያካፍሉት ፣ ከ፲፩—፲፱ ፣ ዴግሬ ፣ ይደርሳል ።

፱ ፤ ደጋው ፣ ግን ፣ ከደጋው ፣ እህልና ፣ ዛፍ ፣ በቀር ፣ ማንኛውንም ፣ አያበቅልም ። ሙቀቱም ፣ ከ፯—፰ ፣ ዴግሬ ፣ እስከ ፣ ዜሮ ፣ ይደርሳል ።

፲ ፤ ስለ ፣ ኢትዮጵያና ፣ በውስጧ ፣ ስለሚኖሩ ፣ ሕዝብ ፣ ከሚነገረው ፣ ከብዙ ፣ በጥቂቱ ፣ ከረጅም ፣ ባጭሩ ፣ ይህ ፣ ይበቃናል ።

## ጥ ያ ቄ ።

የኢትዮጵያ ፣ ጥንታዊ ፣ ወሰኑዋ ፣ ከየት ፣ እስከ ፣ የት ፣ ኖሩዋል ፣ ?

በውስጧ ፣ የሚገኙትን ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የሆኑትን ፣ የከበሩ ፣ ዕቃዎችና ፣ የሚገኙበትንም ፣ አውራጃዎች ፣ ተናገር ።

ይህን ፣ የመሰለ ፣ አገርዋን ፣ ከውጪ ፣ የመጡ ፣ ባዕዳን ፣ ሕዝብ ፣ የያዙበት ፣ ምክንያት ፣ ምን ፣ ይሆን ፣ ?

ጥንት ፣ ምስርን ፣ ጨምረው ፣ የገዙ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ነገሥታት ፣ ስንት ፣ ናቸው ፣ ?

ስለ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ ውበትና ፣ ደግነት ፤ ስለ ፣ መስተንግዶ ፣ በውስጧ ፣ ስላሉ ፣ የጤና ፣ ምንጮች ፣ ስለሚሆኑ ፣ ውሆች ፣ ስለ ፣ ቆላውና ፣ ወይና ፣ ደጋው ፣ ስለ ፣ ደጋውም ፣ አገር ፣ የሙቀትና ፣ የቅዝቃዜ ፣ ልክ ፣ በውስጧም ፣ ስለሚበቅሉት ፣ እህልና ፣ አትክልት ፣ ዘርዝረህ ፣ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

**በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የተጀመረበት ፡ ጊዜና ፡ የነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ድምር ፡ የዘመኑም ፡ ልክ ።**

፩ ፤ መጀመሪያ ፡ ከሰብታህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጲኦሬ ፡ አንደኛ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፪ሺ ፡ ፭፻፵፭ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፹፭ ፡ ዓመት ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ፴፪ ፡ ናቸው ፤ ዘመኑም ፡ ፭፻፷ ፡ ይሆናል ።

፪ ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ መንገሥ ፡ ከጀመሩበት ፡ ከሺ ፱፻፹፭ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ነገሠበት ፡ እስከ ፡ ፱፻፹፪ ፡ ዓመት ፡ አግዓዝያን ፡ ከተባሉ ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ፶፪ ፡ ናቸው ። ዘመኑም ፡ ፩ሺ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

፫ ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከነገሠበት ፡ ከ፱፻፹፪ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ተወለደበት ፡ እስከ ፡ ፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ባዚን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ፳፯ ፡ ናቸው ። ዘመኑም ፡ ፱፻፹፪ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባዚን ፡ ከክርስቶስም ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ነግሦዋልና ፡ ይህ ፡ ሲጨመር ፡ ፱፻፺፩ ፡ ይሆናል ።

፬ ፤ በዘመኑ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከተወለደበት ፡ ከባዚን ፡ ጀምሮ ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡ ዛጔ ፡ እስከ ፡ ፈለሰበት ፡ እስከ ፡ ድልነዓድ ፡ ድረስ ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፱፻፲፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ፺፬ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባዚን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያልተቈጠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፺፫ ፡ ይሆናል ። ዘመኑም ፡ ፱፻፲፪ ፡ (፱፻፳) ዓመት ፡ ይሆናል ። ክርስትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ በነዚሁ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከ፪፻፺፰ ፡ እስከ ፡ ፫፻፴፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በአብርሃና ፡ አጽብሓ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

፭ ፤ ከድልነዓድ ፡ በኋላ ፡ ከመራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ዛጔ ፡) ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ይትባረክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ የዛጔ ፡ ወገኖች ፡ ፲፩ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ። ዘመኑም ፡ ፫፻፵፫ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

፮ ፤ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በኃይል ፡ ወደ ፡ ዛጔ ፡ ዘር ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፵፫ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ከተመለሰበት ፡ ከሺ ፡ ፪፻፵፭ ፡ (ሺ ፡ ፪፻፶፫ ፡) ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጀምሮ ፡ የጎንደር ፡ መንግሥት ፡ እስከሚባለው ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ነገሠበት ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፭፻፶፫ ፡ ዓ. ም . በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ፴፯ ፡ ናቸው ። ዘመኑም ፡ ፫፻፩ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

፯ ፤ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ከነገሠበት ፡ ከሺ ፡ ፭፻፶፫ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፯፻፸፯ ዓ. ም. የጎንደር ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ እስከ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ በጎንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የገዙ ፡ ነገሥታት ፡ ፲፰ ፡ ናቸው ። ዘመኑም ፡ ፪፻፳፬ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

፰ ፤ የጎንደር ፣ መንግሥት ፣ የሚባለው ፣ ከተጨረሰበት ፣ ከሺ ፣ ፲፮፻፳፮ ፣ ዓ. ም. ጀምሮ ፣ ቴዎድሮስ ፣ እስከ ፣ ነገሠበት ፣ እስከ ፣ ሺ ፣ ፲፰፻፵፯ ፣ የገዙ ፣ መሳፍንት ፣ ፲፱ ፣ ናቸው ። በነዚህም ፣ መሳፍንት ፣ ዘመን ፣ ሙሉ ፣ ሥልጣን ፣ ሳያገኙ ፣ ለስሙ ፣ ብቻ ፣ ዘውድ ፣ እየጫኑ ፣ በጎንደር ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ ይቀመጡ ፣ የነበሩ ፣ ትውልዳቸው ፣ ከቀዳማዊ ፣ ምኒልክ ፣ ወገን ፣ የሆኑ ፣ ነገሥታት ፣ ፲፬ ፣ ናቸው ።

፱ ፤ ዘመነ ፣ መሳፍንት ፣ ካለፈ ፣ በኋላ ፣ ከሺ ፣ ፲፰፻፵፯ ፣ እስከ ፣ ሺ ፣ ፲፰፻፹፩ ፣ በኃይልና ፣ በጕልበት ፣ የነገሡ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ነገሥታት ፣ ፫ ፣ ናቸው ። ዘመኑም ፣ ፴፬ ፣ ዓመት ፣ ይሆናል ።

፲ ፤ የሸዋ ፣ መንግሥት ፣ ባላባቶች ፣ ፲፰ ፣ ናቸው ። የግዛታቸውም ፣ ዘመን ፣ ፪፻፸ ፣ ዓመት ፣ ይሆናል ። በግራኝ ፣ ሽብር ፣ ጊዜ ፣ ከአጼ ፣ ልብነ ፣ ድንግል ፣ ልጆች ፣ አንደኛው ፣ አቤቶ ፣ ያዕቆብ ፣ በሸዋ ፣ ቀርቶ ፣ ነበር ። እርሱም ፣ ገራም ፣ ፋሲልንና ፣ ሥግወ ፣ ቃልን ፣ ይወልዳል ። ገራም ፣ ፋሲል ፣ የሱስንዮስ ፣ አባት ፣ ነው ።

፲፩ ፤ ሥግወ ፣ ቃል ፣ የሸዋ ፣ መሳፍንት ፣ አባት ፣ ነው ። የምስፍናው ፣ ግዛት ፣ የተጀመረውና ፣ እየጕላም ፣ የሚነገረው ፣ ከነጋሢ ፣ ክርስቶስ ፣ ወዲህ ፣ ነው ።

፲፪ ፤ እነሆ ፣ ከሥግወ ፣ ቃል ፣ ጀምሮ ፣ ያሉትን ፣ የሸዋ ፣ መሳፍንት ፣ እንደ ፣ ትውልዳቸው ፣ ተራ ፣ ጽፈናቸዋል ።

፲፫ ፤ ሥግወ ፣ ቃል ፣ ወረደ ፣ ቃልን ፣ ይወልዳል ። ወረደ ፣ ቃል ፣ ልብሰ ፣ ቃልን ፣ ይወልዳል ። ልብሰ ፣ ቃል ፣ ከወይዘሮ ፣ ሰንበልት ፣ ነጋሢን ፣ ይወልዳል ። ነጋሢ ፣ ስብስቴን ፣ ይወልዳል ። ስብስቴ ፣ መርድ ፣ አዝማች አብዩን ፣ ይወልዳል ። መርድ ፣ አዝማች ፣ አብዩ ፣ መርድ ፣ አዝማች ፣ አምኃየስን ፣ ይወልዳል ። መርድ ፣ አዝማች ፣ አምኃየስ ፣ ከወይዘሮ ፣ ዕፁብና ፣ መርድ ፣ አዝማች ፣ አስፋ ፣ ወሰንን ፣ ይወልዳል ። መርድ ፣ አዝማች ፣ አስፋ ፣ ወሰን ፣ መርድ ፣ አዝማች ፣ ወሰን ፣ ሰገድን ፣ ይወልዳል ። መርድ ፣ አዝማች ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ ዳግመኛም ፣ ራስ ፣ ተብሏል ፤ ከወይዘሮ ፣ ዘነበ ፣ ወርቅ ፣ ንጉሥ ፣ ሣህለ ፣ ሥላሴን ፣ ይወልዳል ። ንጉሥ ፣ ሣህለ ፣ ሥላሴ ፣ ንጉሥ ፣ ኃይለ ፣ መለኮትን ፣ ይወልዳል ። ንጉሥ ፣ ኃይለ ፣ መለኮት ፣ ከወይዘሮ ፣ እጅግ ፣ አየሁ ፣ አጼ ፣ ምኒልክን ፣ ይወልዳል ።

፲፬ ፤ <u>የዓድዋ ፣ ጦርነት ።</u> አጼ ፣ ምኒልክ ፣ ባ፲፰፻፹፪ ፣ ዓ. ም. የነገሡ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ናቸው ። የአጼ ፣ ምኒልክን ፣ ታሪክ ፣ አስፍተን ፣ ለማየት ፣ የሚመችን ፣ የዓድዋን ፣ ጦርነት ፣ ስንመለከት ፣ ነው ። አጼ ፣ ዮሐንስ ፣ ወዲያው ፣ እንደ ፣ ሞቱ ፣ አጼ ፣ ምኒልክ ፣ ከኢጣልያ ፣ መንግሥት ፣ ጋራ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ ጥቅም ፣ እንዲሆን ፣ ብለው ፣ የተዋዋሉት ፣ ውል ፣ ውሎ ፣ አድሮ ፣ ጕዳት ፣ የሚያመጣ ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። ኢጣሊያኖችም ፣ የሚመች ፣ ጊዜ ፣ ስለ ፣ አጋጠማቸው ፣ ከምጥዋ ፣ እየተንኳተቱ ፣ ሐማሴንን ፣ እንኳ ፣ አልፈው ፣ ወደ ፣ መካከል ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሊንሳፈፉ ፣ ሞክረው ፣ ነበር ። ጣሊያኖች ፣ ሐማሴንን ፣ ወደ ፣ ኋላቸው ፤ ትተው ፣ መረብን ፣ ተሻገሩና ፣ ወደ ፣ መካከለኛው ፣ ትግሬ ፣ እየተስለከለኩ ፣ ገብተው ፣ በስተ ፣ ዓድዋ ፣ አፋዛዥና ፣

በሴላም ፡ በኩል ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ማለታቸውን ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፡ ለአጼ ፡ ምኒልክ ፡ አስታወቁ ። አጼ ፡ ምኒልክም ፡ ወዲያው ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸውንና ፡ ሠራዊቱን ፡ በዐዋጅ ፡ ሰብስበው ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ገሠገሡ ። መጀመሪያም ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የሚሆነው ፡ ክቢ ፡ ጦር ፡ በአንድ ፡ ፊታውራሪ ፡ ድል ፡ ተመትቶ ፡ ቈያቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የካቲት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፰ ፻፹፰ ፡ ዓ. ም. የጣሊያን ፡ ሰልፍ ፡ ወደ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ አሰፍስፎ ፡ መጣና ፡ ዓድዋ ፡ ላይ ፡ ገጥሞ ፡ ተዋጋቸው ። አጼ ፡ ምኒልክም ፡ ጣሊያኖችን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ምርኮኛውንም ፡ ጥርግርግ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ፡አበባ ፡ ተመለሱ ።

፲፭ ፤ የአጼ ፡ ምኒልክን ፡ አልጋ ፡ የያዙ ፡ በፊት ፡ የሴት ፡ ልጃቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ሸዋረገድ ፡ ልጅ ፡ አቤቱ ፡ ኢያሱ ፡ ናቸው ። በኋላም ፡ ሴቲቱ ፡ ልጃቸው ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

### ስለ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

፩ ፤ የተወዳጅ ፡ ንጉማችን ፡ የአጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ትውልድ ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ በአንደኛው ፡ ዘርፍ ፡ ይወርዳል ።

፪ ፤ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፤ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮትንና ፡ ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅን ፡ ሌሎችንም ፡ ይወልዳሉ ። ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ የዶባውን ፡ ባላባት ፡ ደዝጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልን ፡ አግብተው ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ይወልዳሉ ። ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ከወይዘሮ ፡ የሺ ፡ እመቤት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ወለዱ ።

### ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

፫ ፤ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ትውልዳቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ከንጉሥ ፡ ሰሎሞንና ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ዘር ፡ ነው ። በ፲፰፻፹፬ ዓ. ም. ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ሐረር ፡ ኢጀርሳ ፡ ጎሮ ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ተወለዱ ። ያዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሥራችና ፡ የሕዝባቸው ፡ መሪ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጣቸው ።

፬ ፤ ገና ፡ ሕፃን ፡ ሳሉ ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ የሐረርጌ ፡ አውራጃ ፡ ገዢ ፡ ሆኑ ። በዚህም ፡ በተሾሙበት ፡ አውራጃ ፡ ችሎት ፡ ያላቸው ፡ ገዢ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ አሳዩ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ እንዳገኙ ፡ ወዲያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባለ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሆኑ ።

፭ ፤ በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ. ም. መስከረም ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ተባሉ ፤ መጋቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ. ም. ደስ ፡ ባለው ፡ ሕዝባቸው ፡ መኻከል ፡

የመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆኑ ፤ የዘውዱ ፡ በዓል ፡ ግን ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የውጭ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መልክተኞችና ፡ የኢት ዮጵያ ፡ መሳፍንት ፡ ባሉበት ፡ ተከበረ ።

፮ ፤ ምንም ፤ እንኳ ፡ ብዙ ፡ መሰናከል ፡ ቢኖር ፡ ከነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ያላቸ ውን ፡ ብልጫ ፡ አሳይተዋል ። ይልቁንም ፡ ከሌላው ፡ ችሮታቸው ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ለቊስለኞችና ፡ ለሕመምተኞች ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የቤተ ፡ ሳይዳ ሆስፒታልና ፡ በሌ ሎችም ፡ አውራጆች ፡ በሐረር ፤ በደሴ ፤ በትግሬ ፤ በወለጋ ፤ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ሆስፒታል ፡ ማቆማቸው ፡ ነው ።

፯ ፤ ደግሞም ፡ ሕዝባቸው ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕውቀት ፡ የሚደርስበት ፡ በትምህርት ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ በአዲስ አበባ ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በሌሎችም ፡ አውራጃዎች ፡ በሐረር ፤ በደሴ ፤ በትግሬ ፤ በጐጃም ፤ በጂማ ፤ በነ ቀምት ፤ በኢሉባቦር ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ አቋቁመው ፡ እነዚሁ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አሳይተዋል ። በሌላም ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትሻሻል በትን ፡ ሥራ ፡ በየጊዜው ፡ ሠርተዋል ።

፰ ፤ በ፲፱፻፲፱ ፡ ላገርና ፡ ለመንግሥት ፡ ታላቅ ፡ ጠቀሜታ ፡ የሚሰጠውን ፡ የማተ ሚያ ፡ ቤትን ፤ አቆሙ ።

፱ ፤ በ፲፱፻፲፰ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ አደረጉ ፤ በ፲፱፻፲፯ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥንት ፡ የነበራትን ፡ የባሕር ጠረፍ ፡ እንድታገኝ ፡ ለመ ንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አመለከቱ ፡ (ጠየቁ ፡ ) በጥቅምት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፩ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኬሎግን ፡ ውል ፡ ፈረሙ ።

፲ ፤ በዓድዋ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ተመትቶ ፡ የተመለሰው ፡ ጣሊያን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ይመኛት ፡ ነበርና ፡ አኤሮፕላን ፡ ታንክ ፡ የመርዝ ፡ ጭስ እምጥቶ ፡ በገራችን ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ አድርጎ ፡ አገራችንን ፡ አጠፋና ፡ ሴቶቻች ንን ፤ አረከሰ ። ሕዝባችንንም ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ አረዳቸው ፤ የልጆቻችንን ፡ ጠባይና ፡ በጎ ፡ አካሄድ ፡ አበላሸ ፤ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወ ላጅ ፡ በሚቀመጥበት ፡ መኪና ፡ (ካሚዎን ፡ ) በሆቴልና ፡ በሲኒማም ፡ ገብቶ ፡ እንዳይቀመጥ ፡ አጥብቆ ፡ ከለከለ ።

፲፩ ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆንን ፡ ሁሉ ፡ በጣሊያኖች ፡ እጅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ ስንቀበል ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ከቈየን ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱልንና ፤ እኛን ፡ ከባርነት ፤ አገራችንን ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ነጻ ፡ አወጡን ። አሁንም ፡ ነጻነታችን ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ባለማቋረጥ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠራሉ ።

፲፪ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ያደረጉልንን ፡ ውለታ ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ አንረሳውም ። ለሀገራችን ፡ ሲሉ ፡ ባለፈውም ፡ አሁንም ፡ ሥቃይ ይቀ በላሉና ፡ እንወዳቸዋለን ፤ እንታዘዛቸዋለን ። በማፍቀርና ፡ በመታዘዝ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ውለታ ፡ እንድንመልስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ።

## የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፡ ቤት ፡ መንግሥት ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ።

ለታሪክ ፡ የዘመን ፡ ደረጃን ፡ ለመስጠት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በሚከተሉት ፡ ክፍሎች ፡ ተመድቦ ፡ ይነገራል ።

፩ኛ ፡ ክፍል ፤ የነገደ ፡ ኩሳ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡

፪ኛ ፡ ክፍል ፤ የአግዓዝያን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡

፫ኛ ፡ ክፍል ፤ የአግዓዝያን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡

፬ኛ ፡ ክፍል ፤ የቤተ ፡ ዛጔ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡

፭ኛ ፡ ክፍል ፤ የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡

፮ኛ ፡ ክፍል ፤ የጎንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡

፯ኛ ፡ ክፍል ፤ የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡

---

## የ ነ ገ ደ ፡ ኩ ሳ ፡ ዘ መ ነ ፡ መ ን ግ ሥ ት ።

የነገደ ፡ ኩሳ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፪ሺ ፡ ፭፻፹፭ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፫፻፺፯ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከሰብታህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጲአሬ ፡ ፩ኛ ፤ ድረስ ፡ ፶፪ ፡ ነገሥታት ፡ ነግሠዋል ።

## የ አ ግ ዓ ዝ ያ ን ፡ ዘ መ ነ ፡ መ ን ግ ሥ ት ።

የአግዓዝያን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (ሀ)ከአክሁናስ ፡ (ሳባ ፡ ፪ኛ ፡ )አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከሺ ፡ ፱፻፹፭ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ፱፻፹፪ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ፶፪ ፡ ናቸው ፡ ዘመኑም ፡ ፩ሺ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ለ)ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አንሥቶ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ተወለደበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ( ይኸውም ፡ ባዜን ፡ በነገሠ ፡ በ፰ኛ ዓመት ፡) ነገሥታቱ ፡ ፰፯ ፡ ናቸው ፡ ዘመኑም ፡ ፱፻፹፪ ፡ ዓመት ፡ ነው ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በአክሱም ፡ ላይ ፡ ነበር ። (ሐ) ባዜን ፡ ከነገሠበት ፡ ከ፰ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ አንሥቶ ፡ በአብርሃ ፡ ወአጽብሓ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዐተ ፡ ክርስትና ፡ እስከ ፡ መጣበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ነገሥታቱ ፡ ፴፯ ፡ ናቸው ፤ ዘመኑም ፡ ፫፻፵፩ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

## የአግዓዝያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በዘመነ ፡ ክርስትና ።

ሀ) በአብርሃ ፡ ወአጽብሓ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዐተ ፡ ክርስትና ፡ ከመጣበት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አጼ ፡ ግዳዣን ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ (ከ፫፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፰፻፵፬ ፡ ዓ. ም .ድረስ ፡ )ዘመኑ ፡ ፭፻፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ነገሥታቱም ፡ ፶፭ ፡ ናቸው ።

ለ) ከፈላሾች ፡ ወገን ፡ የነገሠቺው ፡ የጉዲት ፡ መንግሥት ፡ (ይኸውም ፡ ከ፰፻፵፬ እስከ ፡ ፰፻፹፬ ፡ ዓ. ም. ድረስ ) ፵ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ሐ) የአክሱም ፡ ንጉሦች ፡ የአጼ ፡ አንበሳውድምና ፡ የአጼ ፡ ድልነአድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ( ከ፰፻፷፯ ፡ እስከ ፡ ፱፻፳፬ ፡ ዓ. ም. ) ፵ ፡ ዓመት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የአክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወድቆ ፡ የዛጌ ፡ መንግሥት ፡ ተነሣ ።

## የቤተ ፡ ዛጌ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

የቤተ ፡ ዛጌ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከመራ ፡ ተክላ ፡ ሃይማኖት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ይትባረክ ፡ ድረስ ፡ ፲፩ ፡ ነገሥታት ፡ የነገሡበት ፡ ፫፻፴፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ዘመኑም ፡ ከ፱፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፲፪፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ነው ።

## የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከነገደ ፡ አግዓዝያን ፡ ሲያያዝ ፡ ከመጣው ፡ ከአክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘር ፡ ነው ። ከአጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አጼ ፡ ሚናስ ፡ ድረስ ፡ ነገሥታቱ ፡ ፳፤ ፡ ናቸው ። (ዘመኑም ፡ ከ፲፪፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፲፭፻፶፩ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ፪፻፹፰ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

## የጎንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

የጎንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ከግራኝ ፡ ሽብር ፡ በኋላ ፡ የሸዋ ፡ ነገሥታት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ከዛወሩበት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ ይቈጠራል ። ጎንደር ፡ የተቈረቈረው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከሚናስ ፡ መንግሥት ፡ ከ፲፮፻ኛው ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ባ፲፯፻፳፪ ፡ ዓ.ም. ቢሆን ፡ ታሪካዊ ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ክፍለ ዘመኑ ፡ በርሱ ፡ ተሰይሟል ።

ሀ) ከአጼ ፡ መለክ ፡ ሰገድ ፡ (ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ) አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ፈጻሜ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ድረስ ፡ (ከ፲፭፻፶፩ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፵፯ ፡ ዓ.ም.) ነገሥታቱ ፡ ፲፮ ፡ ናቸው ።

ለ) ከአጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እስኪዛወር ፡ ድረስ ፡ (ከ፲፰፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፹፩ ፡ ዓ.ም.) ፳ መሳፍንትና ፡ ፫ ፡ ነገሥታት ፡ ገዝተዋል ።

## የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በግራኝ ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ጎንደር ፡ ተዛውሮ ፡ የነበረው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በአንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ሁለተኛው ፡ የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ መዲናውን ፡ በመመልከት ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል

## ከ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ወዲህ ፡ ያሉ ፡

## የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ቊጥር ።

፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ከነገሡት ፡ ከአፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዲህ ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ስሞቻቸውና ፡ የግዛታቸው ፡ ዘመን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተመልክቷል ።

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፤ እስከ ፡ አፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ድረስ ፡ የነበሩትን ፡ ነገሥታት ፡ ስማቸውንና ፡ ቊጥራቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ግን ፡ ከአለቃ ፡ ታየ ፡ በተጻፈው ፡ በክብረ ፡ ነገሥትና ፡ በሌሎች ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ መመልከት ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ እናስገነዝባለን ።

የነገሥታቱ ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የግብር ፡ ስም ፡ በቅንፍ ፡ እየሆነ ፡ ተመልክቷል ።

| ስም ፤ | አባት ፤ | ግዛት ፤ ዓ. መር | ዓመተ ፡ ምሕረት ። |
|---|---|---|---|
| አፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ (ቈስጠንጢኖስ ፡ ) | አፄ ፡ ዳዊት ፡ ፩ኛ ፡ | ፴፬ | ፲፬፻፳፮-፲፬፻፷ |
| አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ | አፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ | --፲ | ፲፬፻፷-፲፬፻፸ |
| አፄ ፡ እስክንድር ፡ | አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ | ፲፮/፳ | ፲፬፻፸-፲፬፻፹፮ |
| አፄ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ | አፄ ፡ እስክንድር ፡ | ፩ | ፲፬፻፹፮- |
| አፄ ፡ ናዖድ ፡ (አንበሳ ፡ ዘፀር) | አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ | ፲፫ | ፲፬፻፹፮-፲፭፻ |
| አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ (ወናግ ሰገድ ፡ ) | አፄ ፡ ናዖድ ፡ | ፴፪ | ፲፭፻-፲፭፻፴፫ |
| አፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ (አጽናፍ ፡ ሰገድ ፡ | አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ | ፲፱ | ፲፭፻፴፫-፲፭፻፶፩ |
| አፄ ፡ ሚናስ ፡ (አድማስ ፡ ሰገድ) | አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ | ፬ | ፲፭፻፶፩-፲፭፻፶፭ |
| አፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ (መለክ ፡ ሰገድ ፡ ) | አፄ ፡ ሚናስ ፡ | ፴፬ | ፲፭፻፶፭-፲፭፻፹፱ |
| አፄ ፡ ያዕቆብ ፡ | አፄ ፡ ሚናስ ፡ | ፯ | ፲፭፻፹፱-፲፭፻፺፭ |
| አፄ ፡ ዘድንግል ፡ | አቤቶ ፡ ልሳነ ፡ ክርስቶስ ፡ እር) ሱም ፡ የሚናስ ፡ ልጅ ፡ ) | ፪ | ፲፭፻፺፭-፲፭፻፺፯ |
| አፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ (ሥልጣን ፡ ሰገድ ፡ ) | አቤቶሁን ፡ ፋሲል (እርሱም ፡ የልብነ ፡ ድንግል ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ | ፳፯ | ፲፭፻፺፯-፲፮፻፳፬ |
| አፄ ፡ ፋሲል ፡ (ዓለም ፡ ሰገድ ፡ ) | አፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ | ፴፮ | ፲፮፻፳፬-፲፮፻፷ |
| አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ አእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ) | አፄ ፡ ፋሲል ፡ | ፲፭ | ፲፮፻፷-፲፮፻፸፬ |
| አፄ ፡ ኢያሱ ፡ ፩ኛ ፡ (አድያም ፡ ሰገድ ፡ ) | አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ | ፳፬ | ፲፮፻፸፬-፲፮፻፺፰ |

| ስም ፤ | አባት ፤ | ግዛት ፤ ዓ. ወር | ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ |
|---|---|---|---|
| አጼ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (ሉል ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ ኢያሱ ፡ (አድያም ፡ ሰገድ ፡) | ፪ | ፲፮፻፺፰-፲፯፻ |
| አጼ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ (አጽራር ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ | ፫/፫ | ፲፯፻-፲፯፻፫ |
| አጼ ፡ ዮስጦስ ፡ | ደጃች ፡ ድል ፡ በኢየሱስ ፡ | ፭ | ፲፯፻፫-፲፯፻፰ |
| አጼ ፡ ዳዊት ፡ ፪ኛ ፡ (አደባር ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ ኢያሱ ፡ (አድያም ፡ ሰገድ ፡) | ፭ | ፲፯፻፰-፲፯፻፲፫ |
| አጼ ፡ በከፋ ፡ (መሲሕ ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ ኢያሱ ፡ (አድያም ፡ ሰገድ ፡) | ፱ | ፲፯፻፲፫-፲፯፻፳፫ |
| አጼ ፡ ኢያሱ ፡ ፪ኛ ፡ (ብርሃን ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ በካፋ ፡ | ፳፭ | ፲፯፻፳፫-፲፯፻፵፯ |
| አጼ ፡ ኢዮአስ ፡ | አጼ ፡ ኢያሱ (ብርሃን ፡ ሰገድ ፡) | ፲፭ | ፲፯፻፵፯-፲፯፻፷፩ |
| አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛ ፡ (ዘዋሕድ ፡ እዴሁ ፡) | አጼ ፡ ኢያሱ (አድያም ፡ ሰገድ ፡) | /፭ | ፲፯፻፷፩ |
| አጼ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (አድ ማስ ፡ ሰገድ ፡) | አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛ ፡ | ፰ | ፲፯፻፷፩-፲፯፻፷፱ |
| ሰሎሞን ፡ | አጼ ፡ ዳዊት ፡ ፪ኛ ፡ | ፪ | ፲፯፻፷፱-፲፯፻፸፩ |
| ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፩ኛ (ፈጻሜ ፡ መንግሥት ፡) | አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛ ፡ | ፭ | ፲፯፻፸፩-፲፯፻፸፯ |

## መ ሳ ፍ ን ት ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ራስ ፡ ዓሊ ፡ (ቅልቁ ፡) | አባ ፡ ሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ | ፬ | ፲፯፻፸፯-፲፯፻፹፩ |
| ራስ ፡ ዓሊጋዝ ፡ | አባ ፡ ሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ | ፭ | ፲፯፻፹፩-፲፯፻፹፯ |
| ራስ ፡ ዐሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ | | ፯ | ፲፯፻፹፯-፲፯፻፺፬ |
| ራስ ፡ ጉግሣ ፡ | መርሶ ፡ በሬንቶ ፡ | ፳፯ | ፲፯፻፺፬-፲፰፻፳፩ |
| ራስ ፡ ይማም ፡ | ራስ ፡ ጉግሣ ፡ | ፬ | ፲፰፻፳፩-፲፰፻፳፭ |
| ራስ ፡ ማርዬ ፡ | ራስ ፡ ጉግሣ ፡ | ፫ | ፲፰፻፳፭-፲፰፻፳፰ |
| ራስ ፡ ዶሬ ፡ | ራስ ፡ ጉግሣ ፡ | /፫ | ፲፰፻፳፰- |
| ራስ ፡ ዓሊ ፡ (ትንሹ ፡) | ደጃች ፡ አሉላ ፡ | ፳፬ | ፲፰፻፳፰-፲፰፻፵፯ |

## ነ ገ ሥ ታ ት ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፪ኛ ፡ (አባ ፡ ታጠቅ ፡) | ቋረኛ ፡ ኀይሉ ፡ ወልደ ፡ ጊዮ ርጊስ ፡ | ፲፭ | ፲፰፻፵፯-፲፰፻፷፪ |

| ስም ፤ | አባት ፤ | ግዛት ፤ ዓ. ወር | ዓመተ ፡ ምሕረት ። |
|---|---|---|---|
| አጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፪ኛ ። | ዋግሹም ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ | ፫ | ፲፰፻፷—፲፰፻፷፫ |
| አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ( አባ ፡ በዝብዝ ፡ ) | ሹም ፡ ተምቤን ፡ ምርጫ ፡ | ፲፰ | ፲፰፻፷፬-፲፰፻፹፩ |
| አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ፪ኛ ፡ ( አባ ዳኘው ፡ ) | ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ (እሳቸውም ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ ) | ፳፬ | ፲፰፻፹፩-፲፱፻፮ |
| ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ፫ኛ ፡ (አባ ፡ ጤና ፡ ) | ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ | ፫ | ፲፱፻፮-፲፱፻፱ |
| ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ | አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ፪ኛ ፡ | ፲፫ | ፲፱፻፱-፲፱፻፳፪ |
| አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቀዳማዊ ፡ ( አባ ፡ ጠቅል ፡ ) | ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ (እሳቸውም ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ) | | |

## የሸዋ ፡ መሳፍትና ፡ ነገሥታት ፡

ይህ ፡ (*) ምልክት ፡ የተደረገባቸው ፡ ሰዎች ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ የማይቈጠርላቸው ፡ የመንግሥት ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፤ በቅንፍ ፡ የተከበበውም ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የነበሩበትን ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ያመለክታል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| * አቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃል ፡ (ዕድሜው ፡ ፷፪) | አቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ | | ፲፭፻፴፱-፲፮፻፩ |
| * አቤቶ ፡ ወረደ ፡ ቃል ፡ (ዕድሜው ፡ ፷፯) | አቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃል ፡ | | ፲፭፻፷፪-፲፮፻፴፱ |
| * አቤቶ ፡ ልብሰ ፡ ቃል ፡ (ዕድሜው ፡ ፷፯) | አቤቶ ፡ ወረደ ፡ ቃል ፡ | | ፲፭፻፹፱-፲፮፻፷፮ |
| አቤቶ ፡ ነጋሢ ፡ | አቤቶ ፡ ልብሰ ፡ ቃል ፡ (እናቱ ፡ ሰንበልት ፡ ፋሪስ ፡ | ፳፱ | ፲፮፻፷፫-፲፮፻፺፪ |
| መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስትያኖስ | አቤቶ ፡ ነጋሢ ፡ | ፲፬ | ፲፮፻፺፫-፲፯፻፯ |
| መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ | መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስት ያኖስ ፡ | ፳፮ | ፲፯፻፯-፲፯፻፴፫ |
| መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ | መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ | ፴፬ | ፲፯፻፴፫-፲፯፻፷፯ |
| መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ወሰን ፡ | መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ | ፴፫ | ፲፯፻፷፯-፲፰፻ |
| መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ | መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ | ፭ | ፲፰፻—፲፰፻፭ |
| ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ | መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ | ፴፭ | ፲፰፻፭-፲፰፻፵ |
| ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ | ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ | ፯ | ፲፰፻፵-፲፰፻፵፯ |